ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 8 የካቲት 2015 ዓ.ም


# የብልፅግና ጉዟችን እየፈተኑ ካሉ አባይት ጉዳዮች አንዱ ሙስናና ብልሹ አሰራር ነው- የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ተመስገን ጥሩነህ

የብልፅግና ጉዟችን እየፈተኑ ካሉ አባይት ጉዳዮች አንዱ ሙስናና ብልሹ አሰራር ነው:: ለዚህም ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቲር ዶ/ር አብይ አህመድ ህዳር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ሙስና የሀገራችን የደህንነት ስጋት መሆኑን በመጥቀስ ተጠያቂነት በማረጋገጥ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግሉን እንዲያስተባብር ብሔራዊ ኮሚቴ የተቋቋመ መሆኑን ለሀገራችን ህዝብ ማሳወቃቸውን ገልፀዋል::



የክልል መንግስታትም ኮሚቴዎችን እንዲሰይሙ በተገለፀው መሰረት ኮሚቴ አቋቁመው የፀረ-ሙስና ትግሉን መቀላቀላቸውን የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ሰብሳቢና የኢፌድሪ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህ አብራርተዋል::

ብሄራዊ ኮሚቴው የፀረ-ሙስና ተቋሙን ስራ ተክቶ የሚሰራ አይደለም:: ሆኖም ችግሩ አሳሳቢ ደራጃ ላይ በመድረሱ ለኮሚሽኑ አቅም በመሆን ቅንጅታዊ አሰራርን በመከተል የከፋ ዝንባሌ እያሳየ የመጣዉን የሙስና ኔትወርክ በማዳከም የሀገር ስጋት በማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በቀጣይ የተቋሙን ተልዕኮ ስኬት ምቹ መደላደል ለመፍጠር ወሳኝ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ብለዋል::



እስካሁን ብሄራዊ ኮሚቴው ከተቋቋመ በኋላ ከህብረተሰቡ 759 ጥቆማዎች የቀረቡ ሲሆን የማጥራት ስራ ተሰርቶ 175 ጥቆማዎች ምርመራ የተጀመረባቸው ሲሆን በ81 ላይ የክስ መዝገብ መከፈቱንና የተከሳሾቹ ብዛት በድምሩ 640 ናቸው::

ለኮሚቴው ቀርቦ የማጣራት ስራ ከተካሄደባቸው ውስጥ እስካሁን ከ2.2 ቢሊዮን ብር በላይ በመንግስትና የህዝብ ሀብት ላይ ጉዳት መድረሱን ማረጋገጥ ተችሏል ብለዋል::

ሰብሳቢው አክለውም ውድ የሆነውን የመንግስትና የህዝብ የመሬት ሀብታችን ስንመለከት፡- 225,885 ካ.ሜ መሬት በምርመራ ላይ ይገኛል ብለዋል::

ሙሰኞች በመጠቃቀም ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እርስ በርሳቸው ወንጀላቸውን ስለሚደብቁ እንጂ የጉዳት መጠኑ የከፋ ይሆናል:: ክልሎችን ቢጨምር ከዚህ በላይ ከፍ እንደሚል ኮሚቴው በግምገማ የተረዳ መሆኑን ገልፀዋል::

ሙስና ረቂቅ ወንጀል ነው፤ ድርጊቱ በደላሎች፣ በመንግስት ሰራተኞችና አመራሮች እንዲሁም ባለሀብቶች በጥቅም ትስስር የተያያዘ በመሆኑ፤ ይህንን የጥቅም ትስስር በመቆራረጥ የሀገርና የህዝብ የሆነውን ሀብት በተገቢው አገልግሎት በመዋል ከፍ ያለ እድገት ለማስመዝገብ ቆራጥነትን ይጠይቃል ብለዋል::

የሙስና ወንጀል የትስስር ገመድ ሳይከብድ በእንጭጩ መበጠስ፣ የወንጀል ችጋኑ ሳይጠነክር መቀልና መለቁ ሳይስፋፋ መግታት ካልቻልን፤ አደጋው የብልፅግና ራዕራያችንን በከንቱ ከማስቀረት ባሻገር ሀገራዊ የሀብት አስተዳደር፣ የፖሊሲ ማውጣትና መቅረፅ እንዲሁም የማስፈፀም ነፃነት የሚጋፋና አቅማችንን ፈተና ላይ የሚጥል መሆኑን ገልፀዋል::

የብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ተመስገን ጥሩነህ በንግግራቸው ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በማጋለጥ ረገድ ሌቦቹ ጠቋሚ ዜጎቻችንን ስለሚፈታተኑ ተገቢውን ጥበቃና ከለላ የማድረግ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አብራርተዋል::

የፀረ-ሙስና ትግሉ ፍሪያማ እንዲሆን ጠቋሚዎች እንደከዚህ ቀደሙ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማሳሰብ የፀረ-ሙስና ኮሚቴው በደረሰው ጥቆማ ልክ ተፈፃሚ እንደሚያደርግ በመተማመን መልካም የፀረ-ሙስና ትግል እንዲሆንልን እመኛለሁ ሲሉ መልክት አስተላልፈዋል::



የብሔራዊ ፀረ-ሙስና ኮሚቴ ውይይት ሰነድ በፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ስራ አስፈፃሚ በአቶ ሀረጎት አብርሃ እና የፀረ-ሙስና ኮሚቴው እስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት ሪፖርት ደግሞ የኮሚሽኑ አስቸኳይ ሙሰና መከላከል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ቀርበው በመድረኩ በተገኙት የክልል፣ የከተማ አስተዳደርና የብሄራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴው አባላት ሀሳብ አስተያየት ተሰጦበታል::

የኮሚቴው አባልና የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በንግግራቸው የቀረቡት ሰነዶች የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ገልፀው፤ እስካሁን የተሰበሰቡትን መረጃዎች በጋራ ለማየትና የቀጣይ ስራችን የጋራ ለማድረግ እንደሆነ አብራርተዋል::

መንግስት በግንባር ቀደምትነት የስነምግባርና የአመለካከት ግንባታ ለማምጣት በትምህርት ዘርፍ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል::

ኮሚሽነሩ አክለውም ኮሚቴው ሙስና የብሄራዊ ስጋት እስከማይሆንበት ደረጃ እንደሚቀጥል ህዝቡ መገንዘብ አለበት ያሉ ሲሆን፤ ኮሚቴው መቋቋሙ ለስራችን ጉልበት በመሆን መነሳሳት ፈጥሮልናል ሲሉ ተደምጠዋል::

የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ሰብሳቢና የኢፌድሪ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ክቡር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ከህብረተሰቡ የሚመጡ ጥቆማዎችን በመለየት የክልል የሆነውን ወደ ክልል የሚላክ መሆኑን ገልፀው፤ ክልሎችም የፌደራል የሆነውን መረጃ መላክ እንዳለባቸው ጠቁመዋል::

የክልል እና የከተማ አስተዳደር ኮር አመራሮች የጥቆማ መረጃ በብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ እንደሚታይ ገልፀዋል::

በሀገር ደረጃ የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በየሶስት ወሩ እየተገናኘ ግምገማዊ ውይይት በማድረግ መረጃ የሚለዋወጥ እንደሆነና በየወሩ ደግሞ የተከናወኑ ተግባርን ለሚመለከተው አካል በመላክ የፀረ-ሙስና ትግሉ ዳር እስከሚደርስ ወደ ፊት እንደሚቀጥል ለተሳታፊዎች መልክት አስተላልፈዋል::

## በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከ1 ሺህ 900 በላይ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘባቸው አመራሮችና ሰራተኞች ከሥራ ተሰናበቱ

ገጽ 2

## በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና በፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ጥቆማ መስጫ ሶፍትዌር ርክክብ ተደረገ

ገጽ 4

## ከሕገ ወጥ ግንባታ ጋር ተያይዞ 12ሺ ብር ጉቦ የተቀበሉ የደንብ አስከባሪዎች መቀጣታቸው ተገለፀ

ገጽ 6

# በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል የጠቋሚዎች እና የምስክሮች ተሳትፎን ማሳደግ አስፈላጊ ነው

## - ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ

በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል የጠቋሚዎች እና የምስክሮች ተሳትፎን ማሳደግ አስፈላጊ ነው - ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ

ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስናን ትግል የጠቋሚዎች እና ምስክሮች ተሳትፎን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሄደ።

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመርሃ ግብሩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስናን ትግል የጠቋሚዎች እና የምስክሮች ተሳትፎን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፤ ሃገር አቀፍ የፀረ-ሙስና ትግልን ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማበረታታት እንደሚያስፈግ ገልፀዋል።









በመድረኩ ላይ የተገኙት በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ድኤታ ክቡር አቶ ተስፋዬ ዳባ ሀገር አቀፍ የሙስና ትግል በአንድ ተቋም ጥረት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ፣ የሁሉም ዜጋ ርብርብ እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ በዋናነት ሕብረተሰቡ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ይኖርብናል ብለዋል።

ሙስናና ብልሹ አሰራርን የማጋለጥ ኃላፊነት ለሕግ አካላት ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ዜጋ የጉዳዩን አስከፊነት በመረዳት ለሃገር አቀፍ የሙስና ትግል የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል ሲሉ መልክት አስተላልፈዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ በበኩላቸው የብሔራዊ ደህንነት ስጋት የሆነውን ሙስና ከመታገል አንፃር ሕብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለሚጠቁሙ አካላትና ምስክሮችን ለሚሰጡ ግለሰቦች ከለላ መስጠትና ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋል።

የመወያያ ሰነዱን በፌድራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙሰና መከላከል ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ማቅረብ ችለዋል።

ዋና ስራ አስፈፃሚው የውይይቱን ዋና ዓላማ ሲገልፁ፤ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል የጠቋሚዎችና ምስክሮች ተሳትፎን በማሳደግ የባለድርሻ አካላት ሚናን ማመላከት እና በሙስና ጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃና ከለላ ተግዳሮቶች ላይ ውይይት በማድረግ የመፍትሄ ሃሳብ ማመላከት ነው ብለዋል። ሙስና ለአንድ ሀገር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖማዊ እና አካባቢያዊ ጉዳት እንደሚያስከትል ገልፀዋል።

በቀረበው መነሻ ሰነድ ተመስርተው አቶ ተስፋዬ ንዋይ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ም/ፕሬዚዳንትና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ቃል አቀባይ እንዲሁም አቶ አብርሃም አያሌው የUNODC Ethiopia ተወካይ ሀሳብ፣ አስተያየት እንዲሁም በመድረኩ ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የቻሉ ሲሆን፤ በመድረኩ ላይ የተገኙት ባለድርሻ አካላትም በሰነዱ ላይ ሀሳብ አስተያየት በመስጠት ሀሳቡን የጋራ ማድረግ ችለዋል።

በቀረበው ሰነድና ውይይት ላይ ተመስርቶ የማጠቃለያ መልክት ያስተላለፉት የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ የፀረ-ሙስና ትግል በስሜት የሚመራ ሳይሆን ጥልቅ የሆነ ጥናትና መተባበርን መሰረት ተደርጎ ከልብ የመነጨ ፍላጎትን የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

የተረጋጋች ሀገር ለመፍጠር ሙስናና ብልሹ አሰራርን በጋራ ልንታገል ይገባል። ሙስናን ለመታገል የተቋማት አመራር ቁርጠኛ ሁነው በሚመሩት ተቋም ውስጥ የሚፈጠሩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ሊፈትሹ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሙስናን ለመታገል የአንድ ተቋም ስራ ብቻ ሳይሆን፥ የዲሞክራሲ ተቋማትና ሌሎች ተቋማት እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በቅንጅት በመስራት ለሀገር ጠንቅ የሆነውን ችግር ልንታገለው ይገባል ብለዋል።

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በማጠቃለያ ንግግራቸው የጠቋሚዎችንና የምስክሮችን ተሳትፎ በማሳደግ አሁን የተጀመረውን ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል በማስቀጠል ሙስና የሀገር ጠንቅ ወደማይሆንበት ደረጃ ማድረስ ይኖርብናል ብለዋል።

ይህ የሚሆነው ተቋማትን የሚመሩ አመራሮች ፓለቲካዊ ቁርጠኝነትን በመውሰድ ሊሰሩ ይገባል ያሉ ሲሆን፤ ህብረተሰቡም ሙስናና ብልሹ አሰራር አሁን ለምናየው ሀገራዊ ችግር አንዱ መንስኤ መሆኑን በመረዳት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ያለማው የጥቆማ መቀበያ ሶፍትዌር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ጠቀሜታው የጎላ ከመሆኑ ባሻገር ጠቋሚዎችና ምስክሮች በቴክኖሎጂ ታግዘው ካለምንም መሳቀቅና መሸማቀቅ ደህንነታቸው ተጠብቆ ጥቆማ እንዲሰጡ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ብለዋል።

ኮሚሽነሩ አክለውም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ በትውልድ የሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ በጋራ መስራት አይነተኛ ሚና መሆኑን ጠቁመዋል።

በመድረክ ውይይቱ ላይ የህዝብ ተወካዮች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ዋና ዳይሬክተር እና ሚኒስቲር ዲኤታዎች፣ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ም/ፕሬዚዳንት፣ የሲቪክ ማህበራት እና የምርመራ ጋዜጠኞች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከ1 ሺህ 900 በላይ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘባቸው አመራሮችና ሰራተኞች ከሥራ ተሰናበቱ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘባቸው ከ1 ሺህ 900 በላይ አመራሮችና የመንግስት ሰራተኞች ከሥራ እንዲሰናበቱና በህግ እንዲጠየቁ ተደርጓል።

የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ አስራት አዳሮ የስድስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ ወቅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በየደረጃው ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቫንት ያስፈልጋል ብለዋል።

ይህንን እውን ለማድረግ በተለይም በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ተቀጥረው ህዝብንና መንግሥትን እየበዘበዙ ያሉ አመራሮችንና ሰራተኞችን የመለየት ሥራ ባለፉት ስድስት ወራት በስፋት መከናወኑን ጠቁመዋል።

በተደረገው ማጣራትም ከ1 ሺህ 900 በላይ አመራሮችና ባለሙያዎች በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ተቀጥረው ተገኝተዋል ብለዋል።

ከእነዚህም 170 ያህሉ በየሴክተሩ ያሉ አመራሮች ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ ባለሙያዎችና የመንግስት ሰራተኞች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በመሆኑም የስራ ቅጥር ውላቸው ተሰርዞ ከሥራ እንዲሰናበቱ መደረጉን ገልጸው፤ በቀጣይም በህግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ አስታውቀዋል።

በተመሳሳይም ከ600 በላይ ተገቢ ያልሆነ የሰው ሃይል የማሟላት ሕገ ወጥ የቅጥር ተግባር መፈጸሙን ማጥራት ተችሏል ብለዋል ኃላፊው።







ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃን የመለየት ሥራ የሀገራችንን የዴሞክራሲና የብልጽግና እሳቤዎች ስኬታማ ለማድረግ ከፐብሊክ ሰርቪስ ሴክተር የሚጠበቅ ተግባር ነው ብለዋል።

ለዚህም በየሴክተሩ የዜጎች ቻርተርና መልካም አስተዳደር ስርዓትን በማስፈን የፐብሊክ ሴክተር ተግባራትን አሻሽሎ በተገቢው መምራት እንደሚገባም አውስተዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ እንዳሉት በፐብሊክ ሴክተር የሚሰማሩ አመራሮችና ባለሙያዎች በእውቀትና በክህሎቱ ብቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በተለይም ተለዋዋጭና እያደገ የመጣውን የተገልጋይ ፍላጎት ለማሟላት ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመራቅ ራሳቸውን በክህሎትና በእውቀት ሊያንጹ ይገባል።

በክልሉ ባሉት ዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የተንዛዛውን የፐብሊክ ሰርቪስ መዋቅር አሰራር በመፈተሽ ለተገልጋዩ ምቹና ውስን የመንግስት በጀትን መቆጠብ በሚስያችል መልኩ ማደራጀት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በዚህም የፐብሊክ ሰርቪሱን ተግባር አጭር፣ ግልጽና ውጤታማ በማድረግ ረገድ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ አሳስበዋል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ተግባር ውጤታማ ሆኖ ህብረተሰቡ ተገቢው አገልግሎት ማግኘት እንዲችል በሚደረገው ስራ ላይ መላው የክልሉ አመራርና ባለሙያዎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩም ምክትል ርእሰ መስተዳድሩ አስገንዝበዋል።

በመድረኩ የዞን፣ የወረዳና ከተማ አስተዳደሮች የፐብሊክ ሰርቪስ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ በመድረኩ የክልል የስራ ሃላፊዎችና ካቢኔዎች፣ እንዲሁም የዞን አስተዳደሪዎችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መታደማቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA


# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**



## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


# ርዕሰ -አንቀፅ

## የተቋማት የስራ አፈፃፀምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ለዘላቂ የፀረ-ሙስና ትግል ወሳኝ ነው!!

ሙስና በአገራችን የሚከናወኑትን የልማት ሥራዎች በማደናቀፍና የተቋማትን የአገልግሎት አሠጣጥ ቀሰ በቀስ እንዲዳከሙ በማድረግ፣ የህግ የበላይነት በመሸርሸር፣ በህግ ጥበቃ የተደረገላቸውን የዲሞክራሲና ሰብአዊ ሙብት ድንጋጌዎች እንዲጣሱ በማድረግ ሕዝባችንን በመንግስት ያለው እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ የሁሉም የመልካም አስተዳደር ችግሮች ቁንጮ ነው።

ይህ የመልካም አስተዳደር ፀር የሆነውን ወንጀል በዘላቂነት ለመከላከል ሕዝባዊ መሰረት ያለዉ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አደረጃጀቶችና ባለድርሻ አካላትን በተገቢዉ ሁኔታ ያሳተፈ የፀረ-ሙስና ትግል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

ስለ ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲሁም መልካም አስተዳደር ችግሮች ስናስብ ጉዳዩን ከመንግስት ተቋማት አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ለይቶ ለማስቀመጥ ያስቸግራል።

ለሙስና ትርጉም የሰጡ ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ተቋማትና አካላት እሳቤን ስንመለከትም ስልጣንን አላግባብ መጠቀም ላይ የሚያተኩር ሆኖ እናገኘዋለን።

በርግጥ ችግሩ በግል ተቋማት ላይ የሚስተዋል ቢሆንም ለሃገራት መፈራረስና ለጦርነት መንስኤ ሊሆን የሚችለው ግን በመንግስት ተቋማት ላይ የሚፈፀም ከትንሽ እስከ ትልቅ የሙስና ቅሌት መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

በሀገራችን በቅርብ አመታት የተስተዋሉ የዕርስ በዕርስ ጦርነትና ግጭቶች መንስኤ ከጀርባው ይሄው ነቀርሳ መኖሩ ሲሆን፤ ችግሩን ለመቅረፍ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ጉዳዩ እስካሁን ብሄራዊ ስጋት ሆኖ ቀጥሏል።

መንግስት ችግሩን ለመቅረፍ ከፌደራል እስከ ክልል ድረስ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በማቋቋም እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም፤ በዘላቂነት ለማጥፋት፣ ብሎም ለመቀነስ ተቋማዊ አሰራርን መፈተሽና ማስተካከል ወሳኝ ጉዳይ ነው።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተቋማትን ግልጽነት ደረጃ በማውጣት አሰራራቸውን በመፈተሽ የስራ አፈፃፀምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ ዘርፍ ተኮር መፍትሄዎችን ለማመንጨት እንቅስቃሴ ጀምሯል።

በተቋማት ለሙስና ስጋት እንደመነሻ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ሁኔታዎችን ማለትም የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ሥርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ-ምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ለተለያዩ የሙስና አይነት መከሰት መንስኤዎች እንደሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።

እነዚህን ምክንያቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ጥናት መዳሰስ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ጥልቅ ዳሰሳ በማድረግ የሙስና መከላከያ ምክረ ሀሳቦችን ለማቅረብ የሚያስችል በፌደራል ተቋማትና የልማት ድርጅቶች የስራ አፈፃፀምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ተጀምሯል።

የዳሰሳ ጥናቱ በርካታ ጉዳዮችን የሚዳስስ፣ የተቋማትን የግልፀኝነት ደረጃ ጥናታዊ በሆነ መንገድ ሊያሳይ የሚችል፣ የግልፀኝነት ደረጃውን ተንተርሶ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ በቀጣይ ለተቋማት መፍትሔዎችን ለማመንጨት እንደ መነሻ ሰነድ ሆኖ የሚወሰድ እንዲሁም ለቀጣይ ለተቋሙ ተግባራት ፍኖተ ካርታ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል በሁሉም የመንግስት የፌደራል ተቋማትና የልማት ድርጅቶች የሚካሄድ የዳሰሳ ጥናት ነው።

ተቋማት ግብር ከፋይ ለሆነው ህዝብ አገልግሎታቸውን፣ የበጀት አጠቃቀማቸውን፣ በጠቅላላው ውስጣዊ አሰራራቸውን ግልጽ ማድረግ በልመና የሚደረግ ሳይሆን ግዴታቸው መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ይህ የተቋማት አሰራር እስካልቀረ ድረስ ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲሁም መልካም አስተዳደር ችግር ይሻሻላል ማለት ጉንጭ ማልፋት ይሆናል።

በርግጥ አንዳንድ ልዩ ተቋማት ለሀገር ደህንነት ሲባል መረጃዎችን ይፋ ለማድረግ የህግ ድጋፍ ያላቸው ይኖራሉ። ሆኖም ሌሎች ተቋማትን የማይመለከት በመሆኑ በተለይ የግዥና ፋይናንስ እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቶችን ለተቋሙ ሰራተኞች እንዲሁም ለህዝብ ይፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ አንጻር ጥናቱ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

ሌላው የጥናቱ ፋይዳ የፀረ-ሙስና ትግሉን በኮሚሽኑ ብቻ ሳይሆን በየተቋማቱ ማስፋት ነው። ሁሌም እንደሚባለው የፀረ-ሙስና ትግል በአንድ ተቋም ብቻ ሚፈታ ችግር ሳይሆን በተቋማቱ አሰራሮችን በማቅናት፣ ግልፀኝነትን በማጠናከር፣ የአመራርና ሰራተኛ የሥነ-ምግባር ክህሎት በማዳበር ሊፈታ የሚችል ውስብስብ ጉዳይ ነው።

መልካም አስተዳደር ሊያሰፍኑ የሚችሉ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ሊከላከሉ የሚችሉ አደረጃጀትና አሰራሮችን በመፈተሽ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ምቹ ሁኔታ የፈጠሩ ተቋማትን መለየት ሲሆን፤ በዚህ ረገድ ደካማ እንቅስቃሴ ያላቸውን በማጠናከር፤ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸውን ተቋማት ደግሞ በማበረታታት ትግሉን በየተቋማቱ ለማጽናት የሚያግዝ ይሆናል።

በመሆኑም የተቋማት ኃላፊዎች፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለጥናቱ መሳካት የማያቋርጥ ድጋፍ በማድረግ በትገበራ ወቅት ለሚካሄዱ ማሻሻያዎች አወንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ይጠበቃል።

ኮሚሽኑም የችግሩን ጥልቀትና ግዝፈት በመረዳት መሰል ንቅናቄዎችን እና ተግባራትን በግንባር ቀደምትነት በመንደፍ ወደ ስራ የሚገባ በመሆኑ በትብብር እና በቅንጅት ሙስናን ከብሔራዊ ስጋት በማውረድ ምንም ስጋት በማያደርስበት ደረጃ ለማስቀመጥ በትጋት የሚሰራ ይሆናል።

# “ባለፉት ስድስት ወራት ከብልሹ አሰራርና ሌብነት ጋር በተያያዘ ከ200 በላይ አመራርና ሰራተኞች ላይ ክስ ተመስርቷል” - ከንቲባ አዳነች አቤቤ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስድስት ወራት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ማጠናቀቂያ መርሃ ግብር ላይ ተገኝተው የማጠቃለያ ንግግር እና የስራ አቅጣጫ የሰጡት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ብልሹ አሰራርና ሌብነትን የመከላከል ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

አገልግሎት አሰጣጥን ከወቅቱ ጋር እንዲሄድ ለማስቻል በርካታ ዘርፎችን የማዘመን እና የተገልጋዩን እርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ስራ እየተሰራ መሆኑንም ገልፀዋል።

ውስጣዊ አንድነትን በማጠናከር አመራራችን ፅንፈኝነትን፣ ጥላቻን፣ የህብረተሰቡን አንድነት የሚንዱ አስተሳሰቦችን፣ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚደረጉ የሚዲያ ዘመቻዎችን እንዲሁም ሌሎች የፓርቲያችን እሳቤ ያልሆኑ አመለካከቶችን በመዋጋት ረገድ እየተሰራ ያለው ስራ ብዙ ቢሆንም፤ አሁንም ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት እና በህቡእ አደረጃጀት የሚደረግ ህገወጥነት ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በቀሪዎች የበጀት ዓመቱ ወራት ያልተከናወኑ ተግባራት ተለይተው በእቅድ ክለሳ እንዲካተቱ በማድረግ የህዝቡን ኑሮ የሚያቀሉ ፕሮጀክቶች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንደሚሰሩም ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።






# በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና በፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ጥቆማ መስጫ ሶፍትዌር ርክክብ ተደረገ

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የበለፀገው የሙስና ጥቆማ መስጫ ሶፍትዌር የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አመራሮች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ርክክብ ተደረገ።

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመርሃ ግብሩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ሃገር አቀፍ የሙስና ትግል የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማበረታታት እንደሚያስፈግ ገልፀዋል::

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የሙስና ትግል ያለኅብረተሰብ ተሳትፎ ከግብ ማድረስ ስለማይቻል ትግሉን በቴክኖሎጂ መደገፍ ግድ መሆኑን ጠቁመዋል።

በዕለቱ ይፋ የተደረገው ሶፍትዌር፥ ዜጎች በየተቋማቱ አገልግሎት ለማግኘት ሄደው ለብልሹ አሰራር ሲጋለጡ እንዲሁም የሙስና ተግባር ሲያጋጥማቸው በስልካቸው ጥቆማ የሚሰጡበት ቴክኖሎጂ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ያለማው የጥቆማ መቀበያ ሶፍትዌር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ጠቀሜታው የጎላ ከመሆኑ ባሻገር ጠቋሚዎችና ምስክሮች በቴክኖሎጂ ታግዘው ካለምንም መሳቀቅና መሸማቀቅ ደህንነታቸው ተጠብቆ ጥቆማ እንዲሰጡ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ብለዋል::

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ድኤታ ክቡር አቶ ተስፋዬ ዳባ ሀገር አቀፍ የሙስና ትግል በአንድ ተቋም ጥረት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ፣ የሁሉም ዜጋ ርብርብ ይጠይቃል ብለዋል::

በዋናነት ሕብረተሰቡ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ይኖርብናል ያሉ ሲሆን፤ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የማጋለጥ ኃላፊነት ለሕግ አካላት ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ዜጋ የጉዳዩን አስከፊነት በመረዳት ለሃገር አቀፍ የሙስና ትግል የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል ብለዋል::

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ሰለሞን ሶካ በበኩላቸው የብሔራዊ ደህንነት ስጋት የሆነውን ሙስና ከመታገል



አንፃር ሕብረተሰቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች መቀበያ ሶፍትዌር በማልማት ለፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስረክበናል ብለዋል::

ዜጎች በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ላይ በሚያገኟቸው አገልግሎቶች ላይ ያላቸውን አስተያየት ወይም የእርካታ መጠንና በአገልግሎት ሂደት የሚገጥማቸው የመልካም አስተዳደር ችግርን የሙስና ጥቆማ ሶፍትዌሩን በመጠቀም በየትኛውም ቦታና በፈለጉበት ሰዓት ጥቆማ ወይም አስተያየታቸውን መስጠት እንደሚችሉ አብራርተዋል::

ይህ የቴክኖሎጂ ስርዓት ደህንነቱ 24 ሰዓት የተጠበቀ መሆኑን ነው ዋና ዳይሬክተሩ የተናገሩት::

በርክክብ ስነ-ስርዓቱ የፌዴራል ሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ መካከል የውል ስምምነት ፊርማ ተከናውኗል::

የጥቆማ መቀበያ ሶፍትዌሩን ቴክኒካል ጉዳዮች በተመለከተ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የቴክኖሎጂ ባለሙያ የሆኑት አቶ ብርሃኑ አለቃ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፤ ሶፍትዌሩ በ5 ሃገርኛ ቋንቋዎች እንዲሁም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በየትኛውም የአለም ክፍል ላይ ሁነው 24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት ይችላል ብለዋል::

ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ከማሳተፍ አኳያም ለአይነ ሥውራን ዜጎች ምቹ በሆነ መልኩ በድምጽ ታግዘው አገልግሎቱን ማግኘት እንዲችሉ ተደርጎ መሰራቱንም ባለሙያው ገልጸዋል::

ሶፍትዌሩ “የሕዝብ አስተያየት መቀበያ ሲስተም - Public Feedback





System” የሚል መጠሪያ ስያሜ እንዳለው የገለጹት አቶ ብርሃኑ፤ ማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የሶፍትዌሩን ዌብሳይት አድራሻ https://epfs.gov.et በመጠቀም አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል ብለዋል::



## ተመስገን አየለ የተባሉ የኮምቦልቻ ከተማ ነዋሪ በባንክ አካውንታቸው በስህተት የገባ 580 ሺህ 680 ብር ለባለቤቱ መለሱ

የሰው ልጅ ብርታትን ከድካም ጥንካሬን ከድክመት ታማኝነትን ከክህደት እውነትን ከውሸት በመሳሰሉ የሰውነት ባህርያትን አሠናስሎ የሚኖር ፍጡር ነው። እንደ ሁኔታዎች መቀያየር እነዚህን ተቃርኖዊ ባህርያት እየቀያየረ ይቀጥላል።

የሰው ልጅ በሰውነት ልክ ኖሯል የሚባለው ግን በርህራሄ ፍቅርን፣ ትህትናን፣ መግባባትን፣ መከባበርን፣ ትጋትን፣ ሰኬትን፣ አሸናፊነትንና ቅንነትን እንዲሁም ታማኝነትንና አርቆ አሳቢነትን ገንዘቡ ሲያደርግ ነው።

ከዚህ በተቃራኒው ሰው ከሰውነት ባህሪው ጎድሏል። ከሰውነት ልክ ወርዷል፤ የምንለው ጭካኔን፣ ጥላቻን፣ ቂም በቀልን፣ ውድቀትን፣ ሰንፍናንና ድካምን እንዲሁም ክፍትን እንደ ቀላል የኑሮ ማሳለጫ ዘይቤ አድርጎ መጠቀም ሲጀምር ነው።

ከላይ እንደመግቢያ የጠቀስናቸው ሀሳቦች ያነሳነው ሰሞኑን በከተማችን የተከሰተውና የታማኝነት ጥግ ያሳዬ የሰውነትን ልክ በተግባር ያስመሰከረ አንድ ምስጉን ሰው ለማስተዋወቅ ነው። አቶ ተመስገን አየለ ይባላ፤ የ40 ዓመት ጎልማሳ ሲሆኑ በኮምቦልቻ ከተማ በቦርከና ክፍለ ከተማ የ012 ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ናቸው።

የካቲት 1ቀን 2015 ዓ.ም አቶ ተመስገን በጧት ተነስተው መደበኛ ስራቸውን ሲከወኑ ወደ ቢሯቸው እያመሩ ሳለ በእጅ ሰልካቸው ላይ የፅሑፍ መልዕክት ይደርሳቸዋል።

መልዕክቱ ከኢትዮ ቴሌኮም የተለመደ መልዕክት ስለመሰላቸው ብዙም ትኩረት ሳይሰጡት ሰራቸውን ይቀጥላሉ። መደበኛ ሰራቸውን ሲከወኑ ቆይተው አምሽተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። እቤት እንዳረፉ በስላካቸው የገባውን የጽሑፍ መልዕክት በጥሞና ሲመለከቱ ያዩትን ማመን ያቅታቸዋል። የአጭበርባሪዎች የማታለያ ዘዴ ሊሆን እንደሚችልም ጥርጣሬ ያድርባቸዋል።

መልዕክቱን ደጋግመው ከተመለከቱ በኋላ የኢትዮጲያ ንግንድ ባንክ ሂሳብ ቁጥራቸውን ደጋግመው በማየት ስህተት አለመኖሩን አረጋግጠው በአካውንታቸው 580 ሽህ 690 ብር ገቢ መሆኑን ያረጋግጣሉ። የጉዳዩን እውነትነት ለማረጋገጥ ወደ ባንክ ሪፖርት በማደረግ ይጠይቃሉ። አቶ ተመስገን አየለ በአካውንታቸው ገቢ የሆነው ብር እስከ አያት ድረስ በስም ተመሳሳይ ከሆነ የአዲስ አበባ ነዋሪ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ብሩን ለባለ ቤቱ በፍጹም ታማኝነት መልሰዋል።

በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑትን አቶ ተመስገን አየለ በስልክ አግኝተን ያነጋገርናቸው ሲሆን ደስታዬ ወደር የለውም፤ ሎተሪ የደረሰኝ ያህል ነው የተደሰትኩት፤ በአሁኑ ጊዜ እንኳን ይህን ያህል ብር ቀርቶ የሞባይል ካርድ በስህተት ሲሞላ የማይመልሱ ሰዎች በበዙበት ወቅት ይህንን በማየቴ በጣም ገርሞኛል ሲሉ ገልጸዋል።

የኮምቦልቻ ከተማ ነዋሪውን አቶ ተመስገን በአካል አግኝተው ቤተሰብ ማድረግ እንደሚፈልጉም ነግረውናል።

አቶ ተመስገን አየለ ብሩን ለመመለስ ምን አነሳሳዎት ሰንል ለጠየቅናቸው ጥያቄ የኔ ያልሆነ ገንዘብ ለራስ ጥቅም ማዋል እምነቴም ስብዕናዬም አይፈቅድም፤ ይህንን በማድረጋቸው እጅግ ደስተኛ መሆናቸውን የኮምቦልቻ ከተማ ኮሙኒኬሽን በፌስቡክ ገፁ አስፍሯል።

## ሙስናን ከመከላከል ረገድ የቤተሰብ እና የማኅበረሰብ ሚና ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ተካሄደ

ኮሚሽኑ "ሙስናን ለመከላከል የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ሚና ማሳደግ በሚል ርዕስ ከሚኒስትሮች፣ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ፣ ከዩኒቨርቲ እና ከክልልና ከከተማ አስተዳደር ኮሚሽነሮች እንዲሁም ከኃይማኖት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል የውይይት መድረክ አካሄደ።



የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ ሙስና በሀገር ደረጃ ብሔራዊ ስጋት በመሆኑ መንግስት አሁን ላይ የተንሠራፋውን ሙስናን ለመከላከል በብሔራዊ የፀረ-ሙስና ትግል የሕግ ማስከበር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኮሚሽነሩ አክለውም ሙስና በዘላቂነት ለመከላከል በትውልድ ሥነ-ምግባር ላይ መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ክቡር አቶ ቀጀላ መርዳሳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር በበኩላቸው፣ "የሀገር ነቀዝ የሆነውን ሙስናን በመከላከል ረገድ የማኅበረሰቡ ሚና የላቀ ነው" ብለዋል።



መልካም ስነምግባር ሀቀኝነትን፣ ቅንነትንና ጥሩነትን የሚያካትት በመሆኑ ቤተሰብና ማህበረሰብ ለስነምግባር ግንባታ ወሳኝነት አለው ያሉ ሲሆን፤ ሙስና ለአንድ ማህበረሰብ ጠንቅ በመሆን ሰላምን በማደፍረስ የሀገርን ዕድገት የሚገታ፣ ትቂቶች የሚበለፁጉበት፣ ብዙሃኑ በችግር የሚሰቃዩበት ነው።

ስለሆነም ቤተሰብ ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ጥሩና መጥፎውን እንዲለዩ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍ ዜጋ መፍጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

ሚኒስትሩ አክለውም፣ ሙስና በሀገር ደረጃ አሳሳቢና የመልካም አስተዳደር ጠንቅ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የራሱን አስተዋፆ ሊያደርግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ሙስናን በመከላከል የቤተሰብና የማህበረሰብ ሚና በሚል የመነሻ ፅሁፍ የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ስራ አስፈፃሚ በአቶ ሀረጎት አብርሃ ቀርቧል።



የውይይት መድረኩ አላማ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ሚናን በማጎልበት፤ ቤተሰብና ማህበረሰብ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የማጋለጥ ሚናውን በሰፊው እንዲወጣ ለማድረግና ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በግልፅ እንዳይታገል የሚያደርጉ ተግዳሮቶች ላይ ውይይት በማድረግ የጋራ የመፍትሄ ሃሳብ ለማመንጨት እንደሆነ አቶ ሀረጎት አብርሃ ጠቁመዋል።

በውይይት መድረኩ የተገኙት ተሳታፊዎች ሀሳብ፣ አስተያየት በመስጠትና የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት በዕለቱ አወያዮች በአማራና በኦሮሚያ ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ከሚሽን ኮሚሽነሮች ምላሽ በመስጠት የጋራ ሀሳብና ግንዛቤ መያዝ ተችሏል።

የመድረኩን የማጠቃቃለያ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል መንግስት ብሔራዊ ስጋት መሆኑን በመረዳት በሀገር ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በማቋቋም ተጠያቂነት የማስፈን ሂደቱ ዕየተሰራ ነው ብለዋል።

ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ ህብረተሰቡ ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ መረጃና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ሌቦችን መጠቆምና መታገል አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል።

በስነምግባር ግንባታ ቤተሰብ፣ የትምህርትና የኃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ሚዲያዎችና ባለድረሻ አካላት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ኮሚሽነሩ ገልፀው፤ የከተማና የክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መሰል መድረኮችን በማዘጋጀት ስነምግባርን መገባትና ሌቦችን ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር እንዳለባቸው አሳስበዋል።

## በጋምቤላ ክልል በተደረገ የኦዲት ማጣራት ጉድለቶች መገኘታቸውን የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት አስታወቀ

የጋምቤላ ክልል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባለፉት ስድስት ወራት ባካሄደው የፋይናንስ ኦዲት 82 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ያልተወራረደ የሰነድ ክምችትና ተገቢ ባልሆነ አካሄድ ወጪ ሆኖ ማግኘቱን አስታወቀ።

የመስሪያ ቤቱ ጀኔራል ዋና ኦዲተር አቶ ኡሞድ ኦቼዶ ለክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ባቀረቡበት ሪፖርት እንዳመለከቱት፤ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ፣ የሰነድ ክምችቱና ሌላም ተገቢ ያልሆነ አካሄድ ወጪ ሆኖ የተገኘው የክልል፣ የዞንና ወረዳ በሚገኙ 44 መስሪያ ቤቶች ነው።

በመስሪያ ቤቶቹ ላይ የተመላከተው ግኝት በ2013 እና በ2014 የበጀት ዓመት በነበራቸው የፋይናንስ አፈፃፀም በተካሄደ የሒሳብ ምርመራ ላይ ነው ብለዋል።

በጋምቤላ ክልል ... ወደ ገጽ 6 የዞረ



# በጋምቤላ ክልል...

ከግኝቶች መካከል ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ከ50 ነጥብ 7 ሚሊየን ብር የሚበልጥ ደግሞ የተሰብሳቢ /ያልተወራረደ/ ሰነድ ክምችት መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንዲሁም ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ ከአገልግሎት ክፍያ ተቀናሽ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ግብር ወደ መንግስት ዝግ አካውንት ሳይገባ ለብክነት ተዳርጎ እንደተገኘ አመልክተው፤ ከ11 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በላይ ደግሞ የተሟላ ሰነድ ሳይቀርብ ተወራርዶ መገኘቱን አስረድተዋል።

በተጨማሪም ከ7 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር በላይ ከደመወዝ ለልማት፣ ለጡረታና ለሌሎች ሰብአዊ ድጋፍ ተቀናሽ ሆነው ፈሰስ ሳይደረጉ ለብክነት ተዳርጎ መገኘቱን የገለጹት ጀኒራል ዋና ኦዲተሩ፤ ከ2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር የመንግስትን ግዥ መመሪያ ባልተከተለ መልኩ ወጪ ተደረጎ መገኘቱን ጠቁመዋል።

ዋና ኦዲት መስሪያ ቤቱ ግኝቶችን ለማሰመለስ ባደረገው ጥረት ከአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር በላይ ተመላሽ ማድረጉን ጠቅሰው፤ ግኝቶችን ለማስተካከል ፍቃደኛ ያልሆኑ ተቋማትን ደግሞ ለምክር ቤቱ በማሳወቅ በኦዲት ፎረሙ አማካኝነት በህግ እንዲጠየቁ ማድረጉን አስታውቀዋል።


ዋና ኦዲተር መስርያ ቤት በቀጣይም የመንግስትና



የህዝብ ሀብት ለታለመላቸው የልማት ግቦች መዋል እንዲችሉ የጀመራቸውን የፋይናንስ ኦዲት ስራዎች አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

የክልል ምክር ቤት የፕላን፣ የበጀት፣ የፋይናንስና የኦዲት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ኡቦንግ ኝል በሰጡት አስተያየት፤ የኦዲት ግኝቶችን ለማስተካከል ከዋና ኦዲት መስሪያ ቤቱ አቅም በላይ በሆኑ የአስፈፃሚ መሰሪያ ቤቶች ላይ ምክር ቤቱ ባቋቋመው የኦዲት ፎረም በህግ የሚጠየቁበት አሰራር መዘርጋቱን ገልጸዋል።

ይህንም መሰረት በማድረግ ባለፉት ስድስት ወራት ዋና ኦዲት መስሪያ ቤቱ አቅም በላይ ሆነው ለምክር



ቤቱ ሪፖርት የተደረጉለትን የኦዲት ግኝቶች በፎረሙ አማካይኝነት በህግ ለመጠየቅ ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

የኦዲት መስሪያ ቤቱ ባለፉት ስድስት ወራት ያከናወናቸው ተግባራት ከመቼውም ጊዜ የተሻሉ ስራዎች መሆናቸውን የገለጹት ደግሞ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ ናቸው።

የኦዲት ግኝቶችን ለማስተካከል በትኩረት መስራት እንደሚገባና ግኝቶች ለማስተካከል ፈቃደኛ ያልሆኑ ተቋማት በህግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ማስታወቃቸውን ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ማህበራዊ ድረ-ገጽ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።

# ከሕገ ወጥ ግንባታ ጋር ተያይዞ 12ሺ ብር ጉቦ የተቀበሉ የደንብ አስከባሪዎች መቀጣታቸው ተገለፀ

ሕገ ወጥ ግንባታ ማስቆም ሲገባቸው 12 ሺህ ብር ጉቦ የተቀበሉ አምስት የደንብ አስከባሪዎች በእስራትና በገንዘብ መቀጣታቸው ተጠቆመ።

የቅጣት ውሳኔውን ያስተላለፈው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የፀረ-ሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው::

ተከሳሾቹ ብሩክ አበበ አድማሱ፣ ሀብታሙ ጂልቻ ደበሌ፣ ሀይሉ ከበደ መቆያ፣ ትእግስት ሰብስቤ ላቀው እና ጫላ ከበደ ጉርሜሳ የተባሉ ግለሰቦች ናቸው::

የዐቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው ተከሳሾቹ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የደንብ ማስከበር ፅ/ቤት ውስጥ የደንብ ማስከበር ኦፊሰር በመሆን እያገለገሉ በነበሩበት ወቅት በየካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 6:00 ሰአት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው ጨሬ ሰፈራ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ወንጀሉን መፈጸማቸውን ነው::

በዚሁ ስፍራ የግል ተበዳይ ጉኡሽ ተስፋየ የተባለው ግለሰብ በመኖሪያ ጊቢ ውስጥ ያለ ግንባታ ፈቃድ ግንባታ ሲያከናውን በስራ ኃላፊነታቸው ስራውን ማስቆም ሲገባቸው ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው ጉቦ መጠየቃቸውን የዐቃቤ ሕግ ክስ አስረድቷል::

1ኛ፣2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በጋራ በመሆን 1ኛ ተከሳሽ ተበዳይን 10 ሺህ ብር ስጠንና ስራውን ትቀጥላለህ ማለታቸውም በክሱ ሰፍሯል::

ተከሳሾቹ በየካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም ከቀኑ ስድስት ሰዓት በድጋሚ ወደ ተበዳይ ቤት ሄደው 1ኛ ተከሳሽ 10 ሺህ ብር ያንሳል ጨምር በማለት መደራደሩን እና 12 ሺ ብር ከተበዳይ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ተቀብለው ከ3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ጋር የተከፋፈሉ መሆኑ በክሱ ተገልጿል::

5ኛ ተከሳሽ ደግሞ የከሰዓት ፈረቃ ላይ የሚሰራ የደንብ ማስከበር ኦፊሰር ሲሆን፥ በተከሳሾች የተበዳይን ግንባታ እንዳይቃወም ተነግሮት 1 ሺህ ብር የተሰጠውና የተቀበለ በመሆኑ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት ጉቦ መቀበል ወንጀል ነው የተከሰሱት::

ዐቃቤ ሕግም ወንጀሉን መፈጸማቸውን የሚያስረዱ ሁለት የሰው ምስክሮችን ጨምሮ የሰነድ ማስረጃዎችን ለፍርድ ቤቱ አቅርቧል::

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የፀረ-ሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ተከሳሾቹ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውንና ከዚህ ቀደም የወንጀል ሪከርድ የሌለባቸው መሆኑን በቅጣት ማቅለያ ወስዷል::

በዚህም ተከሳሾቹን ከ4 ወር እስከ 6 ወር በሚደርስ ቀላል እስራትና እያንዳንዳቸው በ500 ብር እንዲቀጡ መወሰኑን ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የፌስቡክ ገፅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

# ኮሚሽኑ በመንግስት መሥሪያ ቤትና በልማት ድርጅቶች ውስጥ የሙስና ስጋት ጥናት የመረጃ ስብሰባ ሂደት አስመልክቶ ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት አካሄደ

ኮሚሽኑ በመንግስት መሥሪያ ቤትና በልማት ድርጅቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃ ሰብሳቢ ተሳታፊ ከሆኑ ባለሙያዎችና አማካሪዎች ጋር ውይይት አካሄደ::

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በንግግራቸው የጥናቱ ዋና አላማ በ19 ዘርፎች ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን እና ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ ሀሳቦች ለማስቀመጥ እንደሆነ ጠቁመዋል::

አሁን የተሰበሰበውን ጥሬ መረጃ ከሚቀርበው ሪፖርት በመነሳት ሀሳብ አስተያየት በመለዋወጥ ክፍተቶችን በመሙላት ጥራት ያለው ጥቅል ሪፖርት እንደሚዘጋጅ ገልፀዋል።

ለሙስና ሥጋት ጥናቱ የሚሆን የመረጃ አሰባሰብ የአሰራር ሂደትና ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎች በሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል::

በመድረኩ የተገኙት አዲሱ የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው ከኮሚሽኑ ሰራተኞች ጋር ተዋውቀዋል::

ም/ኮሚሽነሩ በመረጃ ስብሰባው ተሳታፊ የሆኑ አመራርና ባለሙያዎችን የቀረበውን ሪፖርት መሰረት አድርገው ማድነቅ የቻሉ ሲሆን፤ ጥናቱ በክልልና በከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሰራተኞች ጋር በመቀናጀት የተሻለ ተግባር ማከናወን ይኖርብናል ብለዋል::

በተቋማት ላይ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ማካሄድ ለተቋማቱ አመራሮችና ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነት በመፍጠር ለቀጣይ ስራችን መልካም አጋጣሚ መሆኑን ገልፀዋል::

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በዘርፍ-ተኮር የሙስና ተጋላጭነት ጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥና በማጥራት ጥቅል ሪፖርት በማዘጋጀት የዘርፉ ባለቤቶችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሚገኙበት ጥናቱ ቀርቦ ውይይት ይደረግበታል ብለዋል::

የዘርፉ ተቋማት ከሪፖርቱ በመነሳት ለስራቸው እንቅፋት የሚሆኑ ብልሹ አሰራሮችን በክፍተት በማሳየትና ምክረ ሀሳብ በመስጠት እንዲሁም ችግር የፈጠሩ አካላት ካሉም ተጠያቂ የምናደርግበት ሂደት መሆኑን ጠቁመዋል::

ስለሆነም የሚካሄደው የሙስና ሥጋት ጥናት የተቋማት የሙስና ቅነሳ ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁና እንዲተገብሩ ከማድረግ በተጨማሪ የሥነምግባር ግንባታ ሥራዎችን ለመሥራት፣ የሙስና መከላከል







ጥናትን ለማካሄድ፣ የጥቅም ግጭት ለመከላከልና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ለማወቅ ለሚደረጉ ሥራዎች ለማከናወን የመረጃ ምንጩ የሚያገለግል ይሆናል ብለዋል::

በቀጣይ የሙስና ስጋት ጥናቱ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በዘርፎች ስር በሚገኙ የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች በማስቀጠል ጥናቱ ሀገራዊ እንደሚሆን መልክት አስተላልፈዋል::

በተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮችን በመለየት፣ የመከላከያ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ ተቋማት የሙስና ሥጋት ቅነሳ ስትራቴጂ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የመረጃ ስብሰባው በ6 አማካሪዎች እና በ9 የቡድን መሪዎች እንዲሁም በ142 ባለሙያዎች በ19 ዘርፎች ስር በሚገኙ በ162 የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች የተሰራ ነው::

ዘርፍ-ተኮር የሙስና ተጋላጭነት ጥናቱ ጥቅል ሪፖርት ተዘጋጅቶ ሲጠናቀቅ የዘርፉ ተቋማት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና አባላት፣ የተቋሙ አመራሮችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ቀርቦ ውይይት የሚደረግበት መሆኑ ተጠቁሟል::

# ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት እየተሰራ መሆኑ ተገለፀ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና ሰነዶች በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት አስታውቋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ኢስሀቅ አብዱልቃድር ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና ሰነዶችን ለማውገዝና ይህንኑ ብልሹ አሰራር የሚፈጽሙ አካላትን ህጋዊ ተጠያቂ ለማድረግ በተዘጋጀው መድረክ ላይ እንደገለጹት የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ችግሩን ለመዋጋት ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ መሀመድ አብዱልአዚዝ በበኩላቸው የሙስናና ብልሹ አሰራር አንዱ አካል የሆነው ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በሀገርና በዜጎች ላይ እያደረሠ ያለው ጫና ከፍተኛ በመሆኑ ኮሚሽኑ ቸግሩን ለመቅረፍ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ድረ-ገፅ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።



# በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሙስናን ለመከላከል ከክትትልና ቁጥጥር ስራው ባለፈ ግንዛቤን ለማሳደግ ትኩረት ተሰጠ

በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከክትትልና ቁጥጥር ስራው ባለፈ ግንዛቤን ለማሳደግ ትኩረት መሰጠቱን በኦሮሚያ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የምስራቅ ቅርንጫፍ አስታወቀ።

ሙስና በአገር ላይ የሚያደርሰውን አደጋ አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራውን በትምህርት ቤቶች፣ በመንግስት፣ በልማትና በህዝባዊ ተቋማት እያከናወነ መሆኑንም ገልጿል።

የኮሚሽኑ የምስራቅ ቅርንጫፍ ኃላፊ አቶ አደም አማን ሙስናና ብልሹ አሰራር በሀገርና በህዝብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የጎላ በመሆኑ በሁሉም መንገድ መከላከል ይገባል ብለዋል።

በተለይ ተማሪዎች ስለ ሙስና ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች በሚገባ እንዲረዱ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠናዎች እየተሰጡ መሆኑን ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ከመምህራን ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን ገልፀው፤ የስነ-ምግባርና ስነ-ዜጋ መምህራን የጎላ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው ብለዋል።



ከስልጠና በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ ያተኮረ የተማሪዎች የጥያቄና መልስ ውድድር በማካሄድ በስነ-ምግባር የታነጸ ትውልድ የማፍራትና ችግሩን ከስሩ የመከላከል ስራ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

በተለይ የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት በህዝብ ተደጋጋሚ ቅሬታ ከሚቀርብባቸው እንደ ትራንስፖርትና መሬት አስተዳደር ያሉ አስር ተቋማት ተለይተው ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በዞኑ የተለያዩ ተቋማት ያሉ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መኮንኖች ሥራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉም በቅርንጫፉ በኩል ተገቢ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑንም አመልክተዋል።

የዞኑ የሲቪል ሰርቪስና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ቡድን መሪ አቶ ዳዊት ደመቀ እንዳሉት፣ በዞኑ የመንግስት ሠራተኞች ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት እየተደረገ ነው። ሠራተኞቹ የሠራተኛ ስነ-ምግባር መመሪያን መሰረት አድርገው የተገልጋይ ፍላጎትን በሚያረካ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ከቀበሌ ጀምሮ ያሉት ባለሙያዎች ሙስናን ለመከላከልና አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን በተፈጠረላቸው ግንዛቤ ታግዘው በመስራታቸው ተገልጋዩ ሲያቀርብ የነበረው ቅሬታ ቀንሷል ብለዋል።



ሙስና የሀገር ሀብት በተወሰኑ ግልሰቦች እንዲመዘበር እድል የሚፈጥርና ሀገርና ህዝብን የሚጎዳ ነው ያሉት ደግሞ በዞኑ የዶባ ወረዳ አስተዳደር ሠራተኛ አቶ አህመድ ኢብሮ ናቸው።

ለህብረተሰቡ ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ አገልግሎት በመስጠት ለጸረ-ሙስና ትግሉ የበኩላቸውን እንደሚወጡ ማረጋገጣቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# አንድ መቶ ሽህ ብር በስህተት ወደ አካውንቱ የገባለት የወልዲያ ከተማ ወጣት ገንዘቡን ለባለቤቱ መመለሱ ተገለፀ

ወጣት ሱሱ መኮነን የወልዲያ ከተማ ነዋሪና የከተማዋ ገቢዎች መምሪያ ሰራተኛ ሲሆን፤ በስህተት ወደ አካውንቱ የገባውን አንድ መቶ ሽህ ብር ለባለቤቱ በመመለስ አርያነት ያለው ተግባር ፈፅሟል።

"ሰው ያልሰራበትን ነገር ማግኘት፣ የለፋበትን ደግሞ ማጣት አለበት ብየ አላምንም። " የሚለው ወጣቱ የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ምሽት 12 ሰአት ላይ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ነጋ ቸኮለ ከሚባል ሰው አንድ መቶ ሽህ ብር እንደገባ መልዕክት ሲደርሰው ወዲያውኑ በግል የፌስቡክ አካውንቱ ግለሰቡ ገንዘቡን እንዲወስድ የማሳወቅ ስራ መስራቱን አስረድቷል።

በንግድ ስራ ተሰማርቶ የሚገኘውና የራያ ቆቦ ወረዳ ነዋሪ የሆነው አቶ ነጋ ቸኮለ የሞባይል ባንኪግ በመጠቀም ለንግድ ደንበኛው ለመላክ አስቦ ብሩን መላኩን አስረድቶ፥ ደንበኛው ብሩ እንዳልደረሰው ሲያሳውቀው ወደ ማን እንደላከው የማጣራት ስራዎችን እየሰራ እያለ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሱሱ መኮነን የተባለ ሰው ጋር መላኩን እና ገንዘቡንም ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ ስልክ ቁጥር ማስቀመጡን በጓደኞቹ እንደተነገረውና፤ የተቀመጠውን ስልክ በመጠቀም ስደውል ብሩን ለመመለስ ፈቃደኛ መሆኑን ሲነግረኝ አለማንኩም ነበር በማለት ስለ ሁኔታው



ያስረዳል።

ወጣት ሱሱ በወልዲያ ከተማ ታላቁ ራስ አሊ ክፍለ ከተማ 2ኛ ፐሊስ ጽ/ቤት በመገኘት ብሩን ለባለቤቱ አስረክቧል።

"ከሀብት በላይ ጥሩ ህሊና ይበልጣል" ያለው አቶ ነጋ ብሩን ለመለሰለት ወጣት ሱሱ ምስጋና አቅርቧል።

የወልዲያ ከተማ ታላቁ ራስ አሊ ክፍለ ከተማ 2ኛ ፖሊስ ጽ/ቤት ሃላፊ ተወካይ ረዳት ኢንስፔክተር ቡሽራ ሰጥቷል ወደ ተቋማቸው በመደወል በስህተት ወደ አካውንቴ ብር ገብቷል፥ ለባለቤቱ መመለስ እፈልጋለሁ ብሎ ያሳወቃቸውን ሱሱ መኮነን አመስግነው፤ ማህበረሰቡ የራስ ያልሆነን ነገር መጠቀም ስህተት መሆኑን ከወጣቱ ልምድ መውሰድ አለበት የሚል መልዕክት ማስተላለፉን ከወልዲያ የፌስቡክ ገፅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ፡ 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት፡ 9555
ድረ ገፅ፡ http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል፡ http://9555pmo.et/
ቴሌግራም፡https://t.me/PMOfeedback
የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

# ቆይታ



**የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች መገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህበረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው::**

**ስለሆነም በዚህ አምድ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እና የስነ-ምግባር ግናባታን ከፍ ለማድረግ አጋዥ የሚሆኑ ሀሳቦችን በማንሳት ሰፋ ያለ ሀሳብ በማሸራሸር ጥልቅ እውቀትና ልምድ ያካባቱ አዋቂና ታዋቂ እንግዶችን በመጋበዝ ለአንባቢያን ያላቸውን አስተማሪ ሀሳብ የሚያፀባርቁበት ነው::**

**የ€€ፀረ-ሙስና« ጋዜጣ የስምንተኛ ዕትም እንግዳችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ስለሺ ናቸው:: የ€€ፀረ-ሙስና« ጋዜጣ ከልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች:: መልካም ንባብ...**

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በአሁኑ ሰዓት ሙስና በሀገራችን ያለው አስከፊነት ምን ያህል ነው ይላሉ?*

ልጅ ዳኔል ጆቴ፡- ሙስና በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን ከኮቪድ እና ከሌሎች ችግሮች የበለጠ የተስፋፋና ያንሰራራ በህብረተሰቡ መካከል ዘልቆ ገብቶ ድህንነት ያመጣና በኢኮኖሚው ዘርፍ ሊኖር የማይገባውን የበታችና የበላይ ልዩነት እርከን የፈጠረ ነው:: በሌላው አለም ደግሞ ኢትዮጵያ የነበራትን ሰላማዊና ከሙስና ነፃ የነበረችውን ሀገር አርቆ እየወሰደ በመሆኑ መንግስት አሁን እየወሰደ ያለው እርምጃ ቢዘገይም አስፈላጊና ተገቢ በመሆኑ በማህበሩና በግሌ የማሰገን መሆኑን እገልፃለሁ::

ሙስና እንደሚታወቀው ድምፅ የሌለው እንደ ድሮን ወይም ጭስ በዬ ህብረተሰቡ ቤት እየገባ ማህበረሰቡን የሚያበጣብጥና ወጣቶቻችንን የሚያበላሽ፣ ሃይማኖት ተቋማትን የሚያናጋ መሆኑ ግልፅ ነው::

*ፀረ-ሙስና ገዜጣ፡- ሙስናን በመከላከሉ ረገድ ወጣቱ ምን ማድረግ አለበት?*

ልጅ ዳንኤል ጆቴ፡- እኔ ባለኝ የተወሰነች እድሜ ያየሁትና በቀጣይ ሊመጣ የሚችለው የሀገራችን ችግር እያስፈራራኝ ያለው ወጣቶች የሙስናን አስከፊነት የሚያስቀጥሉት ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባልና የምንወዳትን እንዲሁም መሰዋት ልንሆን የተዘጋጀንላትን ሀገር በምን አይነት ሁኔታ ልትቀጥል የምትችል መሆኑ ያሳስበኛል::

ይህን በመረዳት ወጣት ልጆቻችን የሙስናን አስከፊነት በመረዳት በማወቅና ባለማወቅ እየቀማመሱት ከሆነ ችግሩን በመረዳት እጃቸውን በመሰብሰብ ከችግሩ ተሳታፊ ባለመሆን መቆጠብ ይኖርባቸዋል::

ሙስናን የለመደ ህብረተሰብ በየትኛውም አቅጣጫ ሀገር የሚያጠፋና የራሱን የወደፊት ህይወት እያበላሸ መሆኑን ወጣቱ መረዳት አለበት:: ኢትዮጵያ በተቻለ መጠን ከሙስናና ብልሹ አሰራር ንፁህ የምትሆነው አሁን ያለው 70 በመቶው የሆነው ወጣቱ ትውልድ ከእንደዚህ ያለ ችግር መቆጠብ ከመቻላቸው ባሻገር ወደ ችግሩ የሚገቡ ሰዎችን በማስተማርም ጭምር ነው::

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ሙስናን ለመከላከል የሀይማኖት ተቋማት ድርሻቸው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?*

ልጅ ዳንኤል ጆቴ፡- በኢትዮጵያ ባሉ ሃይማኖቶች በኦርቶደክስ፣ በሙስሊምና በካቶሊክ እንዲሁም በሌሎች ሃይማኖት ተቋማት ላይ አልፎ አልፎ የሚታዩ ሌብነቶች ይኖራሉ:: ስለዚህ የሀይማኖት አባቶች በየቤትክርስቲያኑ ስለ ሙስናና ብልሹ አሰራር እና ሊያስከትል የሚችለውን ሀገራዊ ችግር በመረዳት ለህብረተሰቡ ማስተማር ይኖርባቸዋል ብየ አስባለሁ::

*ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የሚዲያ ተቋማት ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው ይላሉ?*

ልጅ ዳንኤል ጆቴ፡- ሚዲያ የአንዱን የህበረተሰብ ክፍል ከሌላኛው ጋር የሚያገናኝ ነው:: ሆኖም ግን የሚዲያ ጥሩና መጥፎ አለ:: በአለፉት አስር አመታት ውስጥ ስናይ የነበረው ሚዲያ ውስጥ የሚነገሩትና የሚወሩት ህብረተሰቡን የሚያጋጩና የሚያጣሉ፣ አንዱን ብሔር ከአንዱ ብሔር የሚያጋድሉ፤ በሃይማኖት መካከል የሌለ ጠብ እንዲፈጠርና ያልነበረውን እንደነበር አድረገው ሲዘግቡ እናያን::

ይሄ ትክክል ያልሆነ፤ ሌላ ተልዕኮ ያለውና ሀገር የማጥፋትና ህብረተሰቡን የሚረብሽ ሁኔታ በመሆኑ ሚዲያዎች ወቅታዊ ዜና አቅረቡ ቢባልም ይህን ማስተካከል ግን አለባቸው:: በእኛ ሀገር የተማረው ክፍል በቁጥር ውስን ስለሆነ ለህብረተሰቡ ሚዲያ በሚቋቋምበትና በሚነገርበት ጊዜ በተቻለ መጠን ህብረተሰቡ በሚገባውና ከገባውም በኃላ ያንን አመዛዝኖ የምንወዳትን ኢትዮጵያ ትክክለኛ ትርጉም የሚሰጥበትን አካሄድ ሚዲያው ዘገባ በማደረስ ስነምጋባራዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል::

ዝም ብሎ በመነሳት ድንጋይና ድንጋይን በማጋጨት ለሁለቱ ወገን ግጭት እሳት ተፈጥሮ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ ኢትዮጵያን እንደመሸጥና ማድከም ነውና ሚዲያው መጠንቀቅ አለበት:: ስለዚህ ሚዲያ ላይ ወጥተን ለህብረተሰቡ አንድ ነገር በምንናገርበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ አስፈላጊውንና ትክክለኛውን ዶክመንትና የማያጠራጥር መረጃ ይዞ በመነሳት መዘገብ እንጂ በማህበራዊ ሚዲያና በየቦታው የተገኘውን መረጃ በመያዝ ዜና ሰርቶ መልዕክት ማስተላለፍ ሀገር ላይ ወረራ እንደማድረግና ህዝቡን ከመረበሽ ያላነሰ እንደሆነ ይቆጠራል::

> **“ሥነ-ምግባርን እና ግብረ-ገብነትን ያልተማረ ማንኛውም ወጣት የወደፊቷ ኢትዮጵያ መከራ ነው ሚሆነው”**



ስለዚህ ሚዲያዎች ከዚህ መሰሉ ችግር ተቆጥበው መረጃውን መዝነው ለህብረተሰቡ ማቅረብ አለባቸው:: ህብረተሰቡ ዜናውን እንኳን መስማት ቢፈልግ እንደ ጋዜጠኛው ጠለቅ ብሎ ስላላየው በሚገባውና ወደ ክፋት ወደማሄድበት እና የሰማውን አመዛዝኖ ሀገር የሚገነባበት መሆን እንዳለበት አምናለሁ:: ሚዲያዎች ከስነምግባር ያፈነገጠ መረጃ ለህብረተሰቡ ከማድረስ መቆጠብ አለባቸው:: በሌላ በኩል ሚዲያዎች ሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ ትኩረት አድረገው መስራት አለባቸው::

ከላይ ለገለፅኩት ችግሮች በሙሉ ሙስናና ብልሹ አሰራር ስር ሰዶ ለሀገራችን እድገትና አሁን ላለው ችግር ግንባር ቀደም በመሆኑ ሚዲያዎች ትኩረት ሰጠው መስራት አለባቸው ብዬ አምናለሁ::

*የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና አስተባበሪያ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደስራ መግባቱን ያውቃሉ፤ ከኮሚቴው ምን ይጠብቃሉ? መቋቋሙ ሙስናን ለመከላከል ያግዛል ብለው ያስባሉ?*

ልጅ ዳንኤል፡- አንዱ ትልቅ እርምጃ ነው የምለው በተሰጠው ስልጣንና መመሪያ መሰረት በየደረጃሰው ያሉ ኮሚሽን ቢሮዎች ሰብስቦ በግልፅነት ያለውን ችግር ፣ ከዛም ባሻገር ችግሮች እንዴት መፈታት እንዳለባቸው በጋራ ምክር ማድረጋቸው በጣም ጥሩ ነው:: ሙስናን ስንታገል እንደሙብራት የሚጠፋና የሚበራ መሆን የለበትም:: የሙስና ስራ ህብረተሰቡ አመቱን በሙሉ እንዲረዳውና እንዲሰማው እንዲሁም አብሮም እንዲሳተፍ የሚመከርበት ዘዴ እየተፈለገ መቋረጥ የለለበት ስራ ነው:: በሀገራችን ብዙ ችግሮች አሉ፤ ህብረተሰቡ መሳተፍ የሚችለው በመንግስት በኩል ያለውን ጠካራነት መረዳት ሲችል ነው::

ዛሬ ሙስናን ለመታገል ያለው እንቅስቃሴ ከ6 ወር በኃላ ተረስቶ ሙስናው የሚባባስ ከሆነ ህብረተሰቡ ጥቆማ ለመስጠት የሚኖረው ፍላጎት የቀዘቀዘ ይሆናል:: ነገር ግን መንግስት አሁን በወሰደው ቆራጥነት ከህብረተሰቡ መካከል ገብቶ በተለይ ወጣቱን የመንግስት ተቋሞችን መከላከያም በለው በፈለከው ገብቶ ኮሚሽኑ እየጀመረ ያለውን የፀረ-ሙስና ትግል ሳያቋርጥ ተሳታፊነታቸው እየጠየቀ የሚሄድ ከሆነ ምንም እንኳን ሙስናን ማጥፋት ባይቻልም አሁን ካለበት በጣም ከፍ ባለ ደረጃ ዝቅ እንደሚያደርገው እና ከጊዜም ብዛት ደግሞ ወጣቱ ህብረተሰብ እጁ ንፁህ የማይሆንበት ሁኔታ አይኖርም::

*የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የፌደራል ስነምግባርና የፀረ-ሙና ኮሚሽን የተለያዩ አማራጮችን በመዘርጋት ጥቆማ እየተቀበለ ተግባራት እያከናወነ ነው፤ በዚህ ዙሪያ ምን ሀሳብ አለዎት?*

ልጅ ዳንኤል፡-በእኛ አገር የመጠቆም ልምዱ ባይኖረንም፤ አሁን ግን አገር ሊጠፋ እና ህብረተሰቡ ወደ መጥፎ ሁኔታ እየሄደ፤ አገር መጥፋት ብቻ ሳይሆን በሙስና በኩል በእጅ የማይዳሰስና አስቸጋሪ አገር የሚያጠፋ ውስብስብ ችግር በመሆኑ ህብረተሰቡን እየመጣብህና እንከላከል ብለን ስንጠይቅ ለህብረተሰቡ አዲስ ይሆንበታል:: ህበረተሰቡ ከመጠቆም ሊቆጠብ ይችላል፤ ይህ የሚሆነው ችግሩን ሳይረዳ ቀርቶ ሳይሆን ጓደኛየንና ቤተሰቤን እንዲሁም ጎረቤቴን ለምን እጠቁማለሁ በሚል ነው::

እውነተኛ ኢትዮጵያዊና ለሀገሩ የሚያስብና የሚጨነቅ ከሆነ ሙሰኞችን መጠቆም ይኖርበታል::

የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ የሚረብሽና የሀገርን ኢኮኖሚ የሚያናጋ ከሆነና ከተረዳ ጥቆማውን ማካሄድ አለበት::

ጥቆማው በስልክ፣ በኢሜል፣ በቴሌግራምና በአካልና በደብዳቤ የሚጠቁም ይሆናል:: አንዳንድ ሰው እንደዚህ ያለ ጥቆማ በሚያደርግበት ጊዜ ማንነቱና ስሙ እንዲታወቅ አይፈልግም::

ስለዚህ በመንግስት በኩል ጋራንቲ ማድረግ ይኖርበታል፤ ይህን ማድረግ ከቻለ ህብረተሰቡ ጥቆማ ማድረጉ የማይቀር ነው:: ይህ ውጤታማ የሚሆነው በሚፈጥረው የግንዛቤ መጠን ይወሰናል::

ጥቆማውን በማዘምን ከእጅ ንክኪ ነፃ በማድረግ መሰራት ከተቻለ ለውጥ እንደሚመጣ ማመን ይኖርብናል:: ጥቆማው ከሰው ንኪኪ ነፃ የሆነ መሆንን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የምንፈጥር ከሆነ ጥቆማ የሚሰጡ ሰዎች ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ መስጠት ይችላሉ፤ ጥቆማ የሚቀበሉ ባለሙያዎችም የችግሩ ሰለባ ስለሚሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል::

*የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ ከመንግስት፣ ከፍትህ አካላት፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ከህዝቡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ምን ይጠበቃል?*

ልጅ ዳንኤል፡- ሙስናን ከመከላከል አንፃር መንግስትና በአሁኑ ሰዓት በተለዬ ትኩረት ሰጥቶ ሙስና የስርዓቱ ችግር እልፍም ሲል ይህንን የመልካም አስተዳደር ችግር ህብረተሰቡ በሰፊው እያማረረው ስለሆነ እንፍታው በሚል በቁርጠኝነት ወደ ስራ መግባቱ ጥሩ ነው:: ያቋቋመውን የፀረ-ሙስና ኮሚቴ የተለያዩ ስራወችን እየሰራ በመሆኑ ያለው እንቅስቃሴ በጥሩ በኩል ስለምናየው እስከመጨረሻው መቀጠል ያስፈልጋል:: የኃይማኖት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ከምንም በላይ የስነምግባር ግባታውና የሙስና ትግሉ ላይ የሃይማኖት ተቋማት ከፍ ያለ ድርሻ አላቸው:: የኃይማኖት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ከምንም በላይ የስነምግባር ግባታውና የሙስና ትግሉ ላይ የሃይማኖት ተቋማት አይተኬ ሚና አላቸው:: ስለዚህ በሃይማኖትና ተቋማት የሃማይማኖት ተከታዩን በማስተማር ህብረተሰቡ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ራሱን በመራቅና ልጁቹን ማስተማር አለባቸው። የሃይማኖት አባቶች ትምህርት የመስጠት ሁኔታው ደካማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሙስናና ብልሹ አሰራሩ በዛው ልክ እየጨመረ ይገኛል::

ህብረተሰቡ ለሙሰኞች ጉቦ በመስጠት የሚፈልገውን አገልግሎ ማግኘት ማቆም አለበት። መሆን ያለበት ሌቦችን ለመንግስት አጋልጦ በመስጠትና ለሚመለከተው መስሪያ ቤት በመጠቆም ሃላፊነት መውጣት ይኖርበታል የሚል ሀሳብ አለኝ::

በአጠቃላይ ባለስልጣናቱ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በተሰማሩበት የሙያ መስክ አካባቢ የተለዬ ርብርብ ማድረግ እና ምንድን ነው ከእኔ የሚጠበቀው በማለት ሙስናና ብልሹ አሰራርን መታገል ይኖርበታል፤ የፍትህ አካሉም ሙያውን አክብሮ ኀላፊነት መወጣት አለበት።

ወጣቱ መገንዘብ ያለበት ኢትዮጵያ እድትፈርስ፣ እንድትወድቅ እና እንድንበረከክ የሚፈልጉ ኀይሎች ስላሉ ነቅቶ መጠበቅ አለበት:: እኛ ዛሬ ልጆቻችንን በሚገባ ካላስተማርን፣ ታሪካቸውን አውቀው እንዲያድጉ ካልተደረገ በስተቀር የጠላቶቻችን መሳለቂያ እንሆናለን፤ ሀገራችንንም ወደ ኋላ እናስቀራታለን::ስለዚህ ሁላችንም ጠንክረን መስራት ይኖርብናል።

# ሳይቃጠል በቅጠል

**በተስፋዬ ሻሜቦ**

የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ሥነምግባርን የመገንባት፣ ሙስናን የመከላከልና የፀረ-ሙስና ትግሉን በበላይነት የማስተባበር ሀላፊነት በህግ የተሰጣቸው አካላት ናቸው።

የፀረ-ሙስና ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች መገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፅኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህበረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው።

ኮሚሽኑ የራሱን ህንፃ በማሳደስ እና የዲጂታል አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ በማድረግ ለኪራይ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ ወጪ ማዳን ችሏል።

የስራ ከባቢን ምቹነት በመፍጠር ባለፉት 6 ወራት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። ይሄውም፡- ለ1,686 ሰልጣኞች ዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ግንዛቤ የማሳደግ እና ለ88 ዓቃብያነ ህግና መርማሪ ፖሊሶች በሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ እውቀትና ክህሎት ላይ የአሰልጣኞች (TOT) ስልጠና መስጠት ችሏል።

እንዲሁም ለ250 መከታተያ ክፍሎች የሱፐርቪዥን እና ኢንስፔክሽን ስራ በማከናወን ድጋፍ የተደረገ ሲሆን፤ በፌዴራል ካሉ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በ6 ወር የተከናወኑ ተግባራት በጋራ የተገመገመ ሲሆን፤ በፌዴራል እና በክልሎች 34 ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት መከናወኑ ተመላክቷል።

በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 753,305.66 ብር እና በ157 የፌዴራል ተቋማት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ክፍሎች በተከናወነ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ 805,063,370.00 ብር እንዲሁም በክልሎች 192,039,019.00 ብር የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከሙስናና ብልሹ አሰራር ማዳን መቻሉ የተገለፀ ሲሆን፤ ከ681,340 ካሬ ሜትር ቦታ የከተማና የገጠር መሬት እንዲድን መደረጉ ተጠቁሟል።

በሌላ መረጃ ለኮሚሽኑ ከቀረቡት 637 የሙስና እና የብልሹ አሰራር ጥቆማዎች መካከል 250 የሙስና ወንጀል ያላባቸው ጉዳዮች መሆናቸው ተመላክቷል።

በፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 637 እና በፌደራል ተቋማት በ22 ዘርፎች በሚገኙ መከታተያ ክፍሎች 472 በአጠቃላይይ 1109 ጥቆማዎች ባለፉት 6 ወራት መቅረባቸው ተጠቁሟል።

ከነዚህ መካከል በመሬትና በቤቶች ጉዳይ 452 (41%)፣ በአገልግሎት ጉዳዮች 479 (44%) እና በፋይናንስ ጉዳዮች 130 (12%) እንዲሁም ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች 48 (5%) በዘርፎች የቀረቡ ጥቆማዎች መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።

በተጨማሪም በክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 499 ጥቆማዎች መቅረባቸው የተገለፀ ሲሆን፤ አፈፃፀማቸውን ክትትል በማድረግ የሙስና ወጀል ፈፃሚዎችን ተጠያቂ እያደረጉ መሆኑን ተመላክቷል።

በፌዴራል ተቋማት ከሚገኙ ከፍተኛ፣ መከካለኛ አመራሮችና ባለሙያዎች 23,290 የሚሆኑት ሀብታቸውን በድጅታል አሰራር (በዳርስ ሲስቴም) ያስመዘገቡ ሲሆን፤ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳረሮች 52,357 አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን አስመስግበዋል።

በበጀት ዓመቱ በፌዴራል 127 እና በክልል 398 ሀብት አስመዝጋቢዎችን የማረጋገጥ ስራ መከናወነ መሆኑንና፤ በድምሩ 525 ሀብት አስመዝጋቢዎችን የማረጋገጥ ስራ መከናወኑን ተመላክቷል።

በቀጣይ ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናትን አጠናክሮ በማስቀጠል በጅምር ላይ የሚገኙ ጥናቶችን ማጠናቀቅና የሚሰጡ ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊ እንደሚሆን ትኩረት ተደርገው እንደሚሰሩ የተገለፀ ሲሆን፤ የዘርፎችንና



የፌዴራል ተቋማትን የግልጸኝነት ደረጃ ግምገማ ይካሄዳል።

በሌላ መረጃ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመንግስት መሥሪያ ቤትና በልማት ድርጅቶች ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮችን በመለየት፣ የመከላከያ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ ተቋማት የሙስና ሥጋት ቅነሳ ስትራቴጂ አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማማከር በ21 ዘርፎች በ146 ተጠሪ ተቋማት በድምሩ በ167 ተቋማት ውስጥ የሙስና ሥጋት ጥናት የሚያካሄዱ የኮሚሽኑን የጥናት ባለሙያዎች አሰማርቶ መረጃዎችን እየሰበሰበ ይገኛል። በተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የጥናት ሥራው አጋዥ ሆነው እየተቀሳቀሱ ነው።

የሙስና ሥጋት ጥናቱ የሙስና ወንጀል ምርመራ ሳይሆን በተቋሙ ውስጥ የሙስና ሥጋት ችግር ሊሆኑ የሚችሉ አሠራርና አደረጃጀቶችን በመለየትና የሙስና መከላከል ዕቅድ በማቀድ ለመተግባር የሚያግዝ ነው።

በመሆኑም ተቋማት ያለባቸውን ለሙስና ሥጋት የሆኑ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ለመለየት የሚያግዙ መረጃዎች በመተንተን፣ ደረጃ ለመስጠት እንዲያስችል በተቋሙ ውስጥ ትክክለኛ መረጃዎችን ለመስጠት የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ የሥራ ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን ግንዛቤ ለመፍጠር በጥናት ቡድን የሚፈለጉ ትክክለኛ መረጃዎችን በተጠየቁ ጊዜ መረጃውን እንዲሰጡ ማድረግ ከተቋማት የበላይ አመራር የሚጠበቅ ትብብርና ቁርጠኝነት ሲሆን፤ ወቅታዊና ጥራት ያለው መረጃ የተቋሙን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑ ግንዛቤ በመውሰድ ተቋማት ትብብራቸውን እያሳዩ ይገኛል።

ስለሆነም የሚካሄደው የሙስና ሥጋት ጥናት የተቋማት የሙስና ቅነሳ ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁና እንዲተገብሩ ከማድረግ በተጨማሪ የሥነምግባር ግንባታ ሥራዎችን ለመሥራት፣ የሙስና መከላከል ጥናትን ለማካሄድ፣ የጥቅም ግጭት ለመከላከልና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ለማወቅ ለሚደረጉ ሥራዎች ለማከናወን የመረጃ ምንጩ የሚያገልግል ይሆናል።

በጥናቱ የሙስና ስጋት ያለበትን ደረጃ በመለየት በቀጣይ ስራዎች ትኩረት ተደርጎ ለማከናዎን የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ፣ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የስልጠና ሞጁል እና ፖሊሲና እስትራቴጂ ለማዘጋጀት፣ የተቋማቱን ነባራዊ ሁኔታ ለማወቅ እንዲሁም በተቋማት ላይ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ለማስፈን የሚያግዝ ጥናት መሆኑን ተጠቁሟል።

ዘርፍ ተኮር የሙስና ተጋላጭነት ጥናቱ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት መረጃውን ለመስጠት ፍቃደኛ የማይሆኑ የተቋም ኃላፊዎች ካሉ ልየታ በማድረግ የጥናቱ አንድ ግኝት ሊሆን እንደሚቻል ጠቁመዋል። ይህ ስራ የኮሚሽኑ ዋና ተግባር በመሆኑ መረጃ በመሰብሰብ እና ምልከታ በማድረግ ጥናቱን አደራጅቶ ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

በቀጣይ የሙስና ስጋት ጥናቱ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በዘርፎች ስር በሚገኙ የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች በማካሄድ የሙስና መከላከል ስራው የሚከወን ይሆናል።

## በሀገራችን ሙስና የሚገኝባቸው ዘርፎችና የመከላከያ ዘዴዎች

ሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ባይኖረውም የራስ ያልሆነውን የህዝብና የመንግስት ሀብትና ንብረት ህገወጥ በሆነ መንገድ ጉቦ በመቀበል ወይም በመስጠት፣ በመስረቅ፣ በመዝረፍ፣ ሥልጣን አላግባብ በመጠቀም፣ በማዳለት ለግል ጥቅም ማዋል የሚል ትርጉም አለው።

ሙስና በሁሉም ተቋማት ውስጥ የሚፈፀም አስፀያፊ ተግባር ሲሆን፤ ይህ አስፀያፊ ተግባር በሁሉም ሰው ይፈጽማል።

ሙስና ሀገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ችግርም ነው። ለዚህም ነው አህጉርና ዓለም አቀፍ ሀገራት ሙስናን በጋራ ለመከላከል የጋራ ስምምነት በመፈጸም ወደ ትግል የገቡት። በተለይ ደግሞ በተማረ ሰው የሚፈጸም ሙስና በዕውቀትና ክህሎት ስለሚፈጸም ውስብስብና ረቂቅ ነው።

## በሀገራችን ሙስና የሚስተዋልባቸው ዘርፎች

በሀገራችን በብዛት ሙስና ከሚስተዋልባቸው ዘርፎች መካከል መሬትና የመንግስት ቤቶች አስተዳደር፣ ገቢዎችና ጉምሩክ፣ የመንግስት አገልግሎትና የመንግስት ግዥ እንዲሁም የፍትህ ዘርፉ እንደሆነ ከጥናቶችና ከሚሙጡ ጥቆማዎች መረዳት ይቻላል።

መሬትና የመንግስት ቤቶች አስተዳደር፡- በዚህ ዘርፍ የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ስለሚታይ ብዙውን ጊዜ ሙስና የሚፈጸምበት ዘርፍ ነው። የመንግስትን መሬት ሳይፈቅዳላቸው በራሳቸው ተነሳሽነት ግንባታ የሚፈጽሙ በርካታ ሰዎች አሉ።

በርግጥ በከተማ ውስጥ ባዶ በሆኑ ቦታዎች ላይ ህገወጥ ግንባታ ለሚፈጽሙ ሰዎች ቦታውን በህገወጥ ሽያጭ የሚያስተላልፉ ሰዎች በመኖራቸው ብዙውን ጊዜ ጉዳት እየደረሰበት ያለው ቦታውን የሸጠው ሰው ሳይሆን ግንባታውን የፈጸመው ሰው ቤቱ ሲፈርስበትና ጉዳት ሲደርስበት ይስተዋላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በነበረው ይዞታ ላይ የመንግስትን መሬት ወደራሳቸው የሚጠቀልሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎችን የመንግስት መሬት ወደ ራሱ ይዞታ የሚጠቀልሉት የከተማ አስተዳደር መሬትና መሬት ነክ ጉዳይ የሚሠሩ ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን በጉቦ ወይም በእጅ መንሻ በማስፈቀድ ወይም ለደንብ ማስከበር ጉቦ በመክፈል ነው።

ስለዚህ ባዶ ቦታዎች ህገወጥ ግንባታ እንዲፈጸም የመሬት ሽያጭ በሚፈጽሙና የሚፈቅዱ ሰዎች ላይ ተገቢው የሆነ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

ሌላው ለግንባታ ፈቃድ መስጠት ነው። በመንግስት መሬት ባዶ ቦታ ላይ ግንባታ እንዲፈጸም የይዞታ ካርታና ግንባታ የሚሠጡት በመንግስት ተቋም ውስጥ ያሉ ሠራተኞች በመሆናቸው ፈቃዱን ደግሞ የሚሠጡት ጉቦ ተቀብለው ስለሆነ ግንባታውን ከማፍረስ ባሻገር ፈቃድ በሚሰጡት ላይም እርምጃ መውሰድን ይጠይቃል።

ሙስና ከሚፈፀምባቸው አንዱ የመንግስት ቤት ነው። የቀበሌ ቤት፣ የኮንዶምኔም እና የኪራይ ቤቶች ተጠቃሽ ሲሆኑ፤ ሶስቱም ቤቶች ድልድል ላይ ከበስተጀርባ ሆነው ጉቦ ወይም እጅ መንሻ ተቀብለው ቤት የሚያከራይ፣ ዝውውር የሚፈጽሙና በግንባታ ሰበብ ወደ ግል ይዞታ እንዲለወጥ የሚፈቅዱ በርከታ የመንግስት ኃላፊዎችና ሠራተኞች አሉ።

አንዳንድ ሰዎች ከከተማ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ባለቸው ትስስር የኮንዶምኔም ቤቶችን ሳይፈቅድላቸው ይዘው በማከራየት የሚጠቀሙ፣ ሲደረስባቸው ደግሞ የሚለቁ ሰዎች መኖራቸው ይታመናል።

መንግስት ከተማ አካባቢ የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታትና የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የሚታዩ የሙስና ችግሮች ናቸው። ፕሮጀክቶችን በጥራት አለመፈጸም፣ ላልተሠራ ሥራ ክፍያ መፈጸም፣ ነጋዴዎችንና የመንግስት ሠራተኞችን በጥቃቅንና አነስተኛ በማደራጀት እንደሠሩ ተደርጎ ክፍያ መፈፀም የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው።

ገቢዎችና ጉምሩክ፡- በዚህ ዘርፍ በርካታ የሀገሪቱ የገቢ ምንጭ እንቅስቃሴ ያለበት ዘርፍ በመሆኑ ውስብስብ ሙስና ይሠራበታል።

ከመንግስት ሠራተኞችና ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ወይም በድብቅ ያልተፈቀደና ቀረጥ ያልተከፈለበትን ዕቃዎችን በኮንትሮባንድ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የሙስና ድርጊት ሲሆን፤ በተግባሩም መንግስትንና ህዝብን የሚጎዳ ወንጀል ይፈፀማል።

ሌላው በሙስና ሀገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ዕቃዎችን በአሮጌ ዕቃ በሚል ቀረጥ ማስከፈል ወይም በነፃ እንዲያስገባ በመፍቀድ ለዜጎች መሠረተ ልማትን የሚዘረጋው መንግስት ገቢ እንዲያጣ ያደርጋል።

በተጭበረበረ ሰነድ ሀገር ውስጥ ያስገባው ሰው ዕቃውን ገበያ ላይ በማስገባት በህጋዊ መንገድ ዕቃ ካስገቡት ሰዎች እኩል ሽያጭ በማካሄድ ይከብራል። በሌላ በኩል በገቢ ላይ የሚበየን ግብር ነው። ባለሀብት በመንግስት መመሪያ መሠረት የገቢ ግብር እንዳያስገባ ወጭን በማናር ትርፍን በመቀነስ፣ ግብር እንዳይገብር በማማከር ሙስና መሥራት ወይም የገቢ ግብር ትክክለኛ አለመሆኑ እየታወቃ በሙስና ማረጋገጫ መሥጠት ሀገርንና ህዝብን የሚጎዳ ተግባር ይፈፀማል።

የፍትህ ዘርፍ፡- በዚህ ዘርፍ በርካታ ተቋማት ያሉ ቢሆንም ከህብረተሰብ ጋር በርካታ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው ሙስና ይሰራበታል። ወንጀል የፈፀመን ሰው በጉቦ ይለቀቃል ወይም ከወንጀል ፈፃሚና ከሳሽ ጉቦ በመቀበል ወንጀለኛን በነፃ መልቀቅ ወይም ያለጥፋቱ እንዲቀጣ ይደረጋል። ወንጀለኛ የሆነ ሰው በጥፋቱ መሠረት መከሰስ ሲገባው በዝቅተኛ ወንጀል አንቀጽ በመክሰስ ጉቦ መቀበል ወይም በከፍተኛ ወንጀል አንቀጽ በመክሰስ ከከሳሽ ጉቦ በመቀበል ፍትህ እንዲዛባ ያደርጋል።

ፍርድ ቤት ደላላ ይዞ በመግባት ተከሳሽ ጉቦ እንዲከፍል ቀጠሮ በማራዘም ማንገለታት ወይም አለአግባብ ዋስትና በመከልከል ፍትህ በማዛባት ሀገርና ህዝብ የሚጎዳ ተግባር ይፈፀማል። በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች በጉቦ በርካሽ በመሸጥ ጉቦ መቀበል ወይም በጉቦ በህገወጥ መንገድ ለማይመለከተው ሰው ማስተላለፍ እንዲሁም ማረሚያ ቤት ውስጥ መቆየት ያለባቸው ሰዎች ቀን የግል ጉዳይ እንዲያስፈጽሙና ቤተሰብ ጋር እንዲውሉ በመፍቀድ ሙስናን መፈጸም የመሳሳሉ ችግሮች በፍትህ ዘርፍ የሚስተዋሉ ናቸው።

የሥነ-ምግባር ኮድ ማዘጋጀትና ግንዛቤ መፍጠር፣ የአገልግሎት ስታንዳርድ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማስተዋወቅ፣ በየጊዜው የአፈፃጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፣ በሚታዩት ክፍተቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ መፍትሄ ይሆናል።

የመንግስት አገልግሎት፡- የመንግስት አገልግሎት የሚባሉት መብራትና ውሃ፣ የተለያዩ ፍቃዶች፣ ውሳኝ ኩነት፣ ፓስፖርት፣ ህክምና ወዘተ ናቸው። አገልግሎቱ በነፃ ወይም በክፍያ ሊሠጥ ይችላል። በመሆኑም በነፃም ሆነ በክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሙስና ሥጋት ያለባቸው ናቸው።

የአገልግሎት ፈላጊ ህብረተሰብ አገልግሎቱን በፈጠነ ጊዜ ማግኘት ሲፈልግ ወይም አገልግሎቱን ለማግኘት የማያስችሉና ያልተሟሉ ነገሮች ሲገጥም በጉቦ ወይም በእጅ መንሻ በመስጠት አገልግሎቱን ሊያገኝ ይችላል።

በአገልግሎት ሰጪ በኩል ደግሞ አገልግሎት የሚፈልጉ የህብረተሰብ አካላት በርካታ ሲሆኑበት አገልግሎት አሰጣጡን በማንቀራፈፍ በፍጥነት ለመስጠት ጉቦ የሚያገኝበትን ሁኔታ በደላላ ጭምር ያመቻቻል። በሌላ በኩል ደግሞ የአገልግሎት ፈላጊውን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከቢሮ በመጥፋት፣ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በማቅረብ፣ አርፍዶ በመምጣት አገልግሎት ፈላጊው ሳይፈልግ በግዱ የእጅ መንሻ በመክፈል አገልግሎት እንዲወስድ ያደርጋል።

በተጨማሪም አገልግሎት ሰጪና ፈላጊ በጋራ ስምምነት ህገወጥ ተግባራትን መፈፀም ነው። ይህ ብዙውን ጊዜ አገልግሎት ሰጪው ከተገልጋይ ህብረተሰብ ጋር በመመሳጠር የመንግስት አገልግሎት መስጠት ወይም የመንግስት ሀብት በህገወጥ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ ሥራ የሚሰራበት ነው።

የመንግስት ግዥ፡- በኢትዮጵያ ከመንግስትን ከዓመታዊ በጀት 70 በመቶ እና ከጂዲፒ 14 በመቶ ለግዥ ይውላል። የግዥ ዕቅድ፣ የተጫራች መረጣ፣ የውል አስተዳደርና የክፍያና ኦዲት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፤ እያንዳንዱ ደረጃ ላይ የሙስና ሥጋት አለበት።

የግዥ ዕቅድ ሲዘጋጅ የዕቃው ወይም የአገልግሎት

ሳይቃጠል በቅጠል ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረውን የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት ሲሆን፤ ሀገራችን ከሙስና ወንጀል ጋር ተያይዞ ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ በኮሚሽኑ፣ በፖሊስና አቃበ ህግ የተሰሩና በመሥራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡፡

በመሆኑም ሀሰተኛ ሰነዶችን ከማዘጋጀትና ከመጠቀም እንዲሁም በአደራ የተረከቡትን የመንግስት ንብረት ለግል ጥቅም ከማዋል ጋር በተያያዘ በተፈጸሙ ወንጀሎች ክስ መመስረቱን እና ከ197 መዝገቦች ውስጥም በ28ቱ ላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መተላለፉን፣ በ26ቱ መዝገቦች 44 ተከሳሾች ጥፋተኛ መባላቸውን፣ በ2 መዝገቦችም 3 ተከሳሾች በነጻ መሰናበታቸውን ተመላክቷል፡፡

ከመሬት ወረራ፣ ከካሳ ክፍያና ከመንግስት ቤት ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች (በተለይም በቦሌ፣ ንፋስ ስልክና ለሚኩራ ክፍለ ከተሞች) በተሰራው የህግ ማስከበር ስራ ከ100 በላይ ተከሳሾችን የያዙ ከ10 በላይ መዝገቦች ምርመራቸው ተጠናቆ ክስ መመስረቱና ከ50 በላይ መዛግብት በምርመራ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ከ14ኛ ዙር የኮንደሚኒየም እጣ አወጣጥ ጋር ተያይዞ በተፈፀሙ የማጭበርበር ወንጀሎች ላይ እንዲሁም የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተም ከመሬትና የመንግስት ቤት አግልግሎት ጋር በተያያዘ እስከ 3.5 ሚሊየን ብር ድረስ ጉቦ ጠይቀው በተቀበሉ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞችና ተባባሪዎቻቸው ላይ በከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱን የተናገሩት አቶ ገብሩ፤ የአርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጅ እንደሆኑ በማስመሰል በ23 ካርታ መብት በመፍጠር 7754 ካ.ሜ የሆነ የመንግስት መሬት በህገ-ወጥ መንገድ በሰጡና በወሰዱ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ አመራሮች፣ ሠራተኞችና ተጠቃሚዎች በድምሩ 43 ተከሳሾች ላይ ምርመራ ተጠናቆ ክስ መመስረቱንም ተጠቁሟል፡፡

የልማት ተነሺ ሳይሆኑ እንደሆኑ በማስመሰል በህገ-ወጥ መንገድ 11 የኮንደሚኒየም ቤቶችን ወስደዉ በሸጡ የቤቶች አስተዳደር አመራሮች፣ ሠራተኞችና ደላሎች በድምሩ 24 ተከሳሾች ላይ ፤በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 02 በአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቤት የይዞታ መጠኑ 1122 ካ.ሜ የሆነውን ስም ለማዞር አገልግሎት ከጠየቁት ግለሰብ ላይ 3.5 ሚሊዮን ብር በመጠየቅ 1.5 ሚሊዮን ብር በተቀበሉ የቂርቆስ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር የመሬት ዝግጅት ባለሙያ እና ግብረአበሮቹ ላይ ምርመራዎቹ ተጠናቀው በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ክስ እየተዘጋጀ እንደሚገኝ እንዲሁም ከቤተመንግስት ግንባታ (በተለምዶ ጫካ ፕሮጀክት እየተባለ የሚጠራ) ልማት ጋር ተያይዞ የልማት ተነሺ በማስመሰል ከ7 ሚሊዮን ብር በላይ ካሳ በከፈሉና የካሳዉ ተጠቃሚ በሆኑ ተጠራጣሪዎች ላይ መዝገብ ተከፍቶ ምርመራ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

ከፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ጋር በተያያዘ ያላቸውን ስልጣን ተገን በማድረግ የባለሀብቶችን እና ድርጅቶቻቸውን የባንክ ሂሳብ አስቀድሞ በማጥናትና መረጃዎችን በመውሰድ በማስፈራራት ከባለሀብቶቹ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮች ገንዘብ እንዲከፍሉ በመጠየቅ የማይከፍሉ ከሆነ ደግሞ የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ምርመራ አድርጎ ጉዳዩን ለፖሊስ የሚያስተላልፍ መሆኑን በመናገር ከባለሀብቶች በርካታ ሚሊዮን ብሮችን በመቀበል ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ የፋይናንስ ደህንነት ሰራተኞች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱን እንዲሁም በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ተገልፃል፡፡



ከፋይናንስ ዘርፍ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተም በህይወት የሌሉና ውጪ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በባንክ ያላቸውን ለረጅም ጊዜ ሳይንቀሳቀስ የቆየ ሂሳብ ደንበኞቹ እንዳሉና እንደቀረቡ በማስመሰል፣ሀሰተኛ ቼኮችን፣ ውክልናዎችን፣ መታወቂያዎችን፣ ሲፒኦዎችን በመጠቀምና የይለፍ ቃል ስርቆት በመፈፀም በተለያዩ ባንኮች ውስጥ የሚገኝ ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ አጭበርብረው በወሰዱ የባንክ ሰራተኞች፣ ግለሰቦችና ተባባሪዎቻቸው ላይ ምርመራ ተጣርቶ አብዛኞቹ ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክሶች መመስረቱ ተመላክቷል፡፡

ከገቢ ዘርፍ ጋር ተያይዞ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተም ምንም አይነት የውጭ ሀገር የጉዞ ታሪክ ሳይኖራቸው ከውጭ ሀገራት የውጭ ሀገር ገንዘብ ይዘው እንደመጡ በማስመሰል ገንዘቡን እያሳወቁ/ዲክላራሽን ሰነድ ላይ በመመዝገብ በሀገር ውስጥ በህገ- ወጥ መንገድ የተገኘን የውጭ ሀገር ገንዘብ ህጋዊ በማድረግ ከ5 ሚሊዮን ዶላር በላይ መንግስትን ጥቅም ባሳጡ 39 የጉሙሩክ ኮሚሽን ቦሌ ኤርፖርት ቅ/ፅ/ቤት ሰራተኞችና ግለሰቦች ላይ ላይ ምርመራ ተጠናቆ ተከሳሾችን የመያዝና የክስ ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝ እንዚህና በርካታ ተግባራት መከናዎናቸውን አቶ ገብሩ ተናግረዋል፡፡

ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ ኤልሻዳይ የልማት ተራድኦ ድርጅት እና የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች በፈፀሙት በሌሎች ተረጂዎች ስም ከ1 ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ የእርዳታ እህል፣ ቁሳቁስና ገንዘብ በመውሰድ ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ 13 ተከሳሾች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀልና ህገ-ወጥ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ክስ ተመስርቷል ሲሉ ዳይሬክተር ጀነራሉ የገለጹ ሲሆን፤ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በተፈጸሙ በርካታ ወንጀሎች ላይ ክስ መመስረቱንና በምርመራ ሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮችም መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

በሌላ መረጃ ከ522 ሺህ በላይ የአሜሪካ ዶላር በማሸሽ ሀገሪቷን የውጭ ምንዛሬ አሳጥተዋል የተባሉ ነጋዴዎችና የጉምሩክ ሰራተኞች የሙስና ወንጀል ክስ ቀረበባቸው፡፡ ክሱ የቀረበባቸው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው፡፡

ተከሳሾቹ ስድስት ሲሆኑ÷ ከዚህ በፊት በሌሎች ሁለት መዝገቦች በተመሳሳይ ተግባር በሙስና ወንጀል የተከሰሱት የጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቦሌ ቅርንጫፍ ሰራተኞች ወተቱ አበበ እና አዲስ አለም ደረሰ ይገኙበታል፡፡

ሌሎቹ ተከሳሾች ነጋዴዎች ሲሆኑ÷ አቶ ሙክታር መህመድ ያሲን፣ መሰረት ንጉሴ፣ ወይዘሮ ሲትራ መሀመድ እና በተመሳሳይ የሙስና ወንጀል ተከሶ ማረሚያ ቤት የሚገኘው ዮናስ አምሳሉ ናቸው፡፡

ተከሳሾቹ የተሳትፎ ደረጃቸው ተጠቅሶ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አድርጎ በማቅረብ እና ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሲሰሩ ከአስመጪ ነጋዴዎች ጋር በጥቅም በመመሳጠር በተለያየ ጊዜ ነጋዴዎቹ የጉዞ ታሪክ ሳይኖራቸው እንዳላቸው በማስፈር እና ከውጭ ሀገር ያላስገቡትን ዶላር እንዳስገቡ አስመስለው ዲክሌር አድርገዋል ተብለው ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

ከ3ኛ እስከ 6ኛ የተጠቀሱ ነጋዴዎች ደግሞ በተለያየ መጠን ከጥቁር ገበያ የሰበሰቡትን ከ522 ሺህ 100 የአሜሪካ ዶላር በላይ ከውጭ ሀገር እንዳስገቡ በማስመሰል እና ሀሰተኛ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ሰነድ በመጠቀም በጉምሩክ ሰራተኞች ዲክሌር በማስደረግ ገንዘቡን በማሸሽ ለግል ጥቅም በማዋል በመንግስትና በህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ተብለው ነው የተከሰሱት፡፡

ከስድስቱ ተከሳሾች መካከል በሌላ ተመሳሳይ ተግባር በሙስና ክስ ወንጀል የተከሰሱት 1ኛ፣ 2ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ዛሬ በችሎት አልቀረቡም፡፡ ቀሪ ተከሳሾች ግን ችሎት ቀርበው ክሱ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

ክሱ በችሎት በንባብ የተሰማ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረቡ ተከሳሾች የክስ መቃወሚያ ካላቸው ለመጠባበቅ ለመጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ቀጥሯል፡፡ ላልቀረቡ ተከሳሾችም መጥሪያ እንዲደርስ መታዘዙን ተገልፃል፡፡

በሌላ መረጃ የአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 05 የወሳኝ ኩነት ጽ/ቤት ሲስተም አድሚኒስትሬተር እና የአቃቂ ቃሊቲ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የቅየሳ ባለሙያን ጨምሮ አምስት ተከሳሾች የቀረበባቸው ክስ በችሎት በንባብ መሰማቱ ተጠቁሟል፡፡

ተከሳሾቹ 1ኛ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የወሳኝ ኩነት ጽ/ቤት ሲስተም አድሚኒስትሬተር ዳንኤል ተስፋዬ፣ 2ኛ ተከሳሽ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ረዳት የቅየሳ ባለሙያ ያሬድ በየነ ዴንሳ፣ 3ኛ ተከሳሽ የዱከም ነዋሪ የሆነው አድማሱ ሙላቱ እና በግል ስራ ይተዳደራሉ የተባሉት 4ኛ ተከሳሽ እስራኤል ደጀኔና 5ኛ ተከሳሽ ብርሃኑ ዳግም ናቸው፡፡

ተከሳሾቹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ) አንቀጽ 33 እና የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9(1) (ሐ)(2) በመተላለፍ በአራት ተደራራቢ ክስ በየተሳትፎ ደረጃቸው ተጠቅሶ ቀርቦባቸዋል፡፡

በተለይም በአንደኛው ክስ ላይ እንደተጠቀሰው፣1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ከ3ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 272 ተብሎ የተመዘገበ የግል ተበዳይ ግለሰብን መኖሪያ ቤት በህገወጥ መንገድ በሀሰተኛ ሰነድ በመሸጥ ለግል ጥቅም አውለዋል ተብለው ተከሰዋል፡፡

በዚህም 1ኛ ተከሳሽ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ምዝገባና የመታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 3/2010 ድንጋጌን በመተላለፍ በግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም በወረዳው ኗሪ ላልሆነ 3ኛ ተከሳሽ ለሆነው አድማሱ ሙላቱ በሀሰተኛ ስም ማለትም ገ/እግዛብሔር ገ/ማርያም በሚል በሀሰት ስም የኗሪነት መታወቂያ መስጠቱ በክሱ ተጠቅሷል፡፡

2ኛ ተከሳሽ ደግሞ በመስከረም 25 ቀን 2015 ዓ/ም የይዞታ የቦታ አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ አዘጋጅቶ ለ3ኛ ተከሳሽ በመስጠት ለአገልግሎቱ ከ3ኛ ተከሳሽ በአራተኛ ተከሳሽ በዳሸን ባንክ በተከፈተ ሒሳብ አጠቃላይ 350 ሺህ ብር ጉቦ በማስገባት ያልተገባ ጥቅም የተቀበለ መሆኑ በክሱ ተጠቅሷል፡፡

በአጠቃላይ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የስራ ሃላፊነታቸውን ለህገወጥ ተግባር በመጠቀም በወንጀሉ ልዩ ተካፋይ በመሆን እርስ በርስ በመመሳጠር የቤት ሽያጭ ውል በመፈጸም ያልተገባ ጥቅም አግኝተዋል ተብለው ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በከባድ ሙስና ወንጀል ነው የተከሰሱት፡፡

በሁለተኛ ክስ ደግሞ በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበ ሲሆን÷ ተከሳሹ ከ2ኛ እና ከ1ኛ ተከሳሾች ያገኘውን መረጃ እና ሀሰተኛ ሰነድ በመጠቀም በሐምሌ 11 ቀን 2014 ዓ/ም በአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 05 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 272 የሆነውን የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤትን በነሃሴ 4 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠኝ የይዞታ ማረጋገጫ ነው በማለት ትክክለኛውን ካርታ ከማህደር በማስወጣት በሀሰተኛ ስም የተሰራውን ካርታ ወደ ማህደር እንዲገባ ማስደረጉ በክሱ ተጠቅሷል፡፡

ከዚህም በኋላ በፌደራል ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ቅርንጫፍ 7 ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ለሌላኛዋ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ቤተልየም ወጋየሁ ሙሉ የውክልና ስልጣን በመስጠት በጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ/ም በመንደር የቤት ሽያጭ ውል በ11 ሚሊየን 500 ሺህ ብር በመስማማት በቅድመ ክፍያ 5 ሚሊየን 300 ሺህ ብር የወሰደ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

በተጨማሪም ይኸው 3ኛ ተከሳሽ በሃሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶችን መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል እንዲሁም በሌላ ሰው ስም በሀሰት በመጠቀም ያለፍቃድ ስምን በመለወጥ ወይም በሌላ ሰው ስም መጠራት የደንብ መተላለፍ ወንጀል ተከሷል፡፡

በሌላኛው ክስ ደግሞ ከ3ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር በተጠቀሱ ተከሳሾች ላይ በህገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ድንጋጌን በመተላለፍ በተለያዩ ቀናቶች የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ ከባንክ ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅም አውለዋል ተብለው ተከሰዋል፡፡

ከ4ኛ ተከሳሽ በስተቀር ሁሉም ተከሳሾች ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን÷ ችሎቱም በዓቃቢ ህግ ተሻሽሎ የቀረበውን ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስን በንባብ አሰምቷል፡፡

ክሱን በንባብ ያሰማው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5 ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው፡፡

ክሱ በንባብ ከተሰማ በኋላ ተከሳሾቹ "ወንጀሉን አልፈጸምንም "ሲሉ ገልጸው የዕምነት ክህደት ቃላቸውን ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡ ከሳሽ ዐቃቢህግ በበኩሉ ለወንጀሉ መፈጸም የሚያስረዱ ምስክሮች ይሰሙልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ችሎቱም የዓቃቢህግ ምስክርን ለመጠባበቅና ለመጋቢት 4 ቀን 2015 ዓ/ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ 4ኛ ተከሳሽ የጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ትዕዛዝ መሰጠቱ ተጠቁሟል፡፡

በሌላ መረጃ ከ492 ሺህ በላይ የአሜሪካ ዶላር በማሸሽ ሀገሪቷን የውጭ ምንዛሬ አሳጥተዋል ተብለው የተጠረጠሩ ሶስት አስመጪ ነጋዴዎች በቁጥጥር ስር ውለው ፍርድ ቤት መቅረቡ ተጠቆመ፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ወይዘሮ ሲትራ መህመድ፣ ዮናስ አምሳሉ እና ሙክታር መህመድ ያሲን ናቸው፡፡

ተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ስር አውሎ የምርመራ ስራውን እያከናወነ የሚገኘው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ ከጉሙሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የተወሰኑ ሰራተኞች ጋር በጥቅም በመመሳጠር ከጥቁር ገበያ የተሰበሰበ የውጭ ምንዛሬን ከውጭ ሀገር እንዳስገቡት በማስመሰል ሀሰተኛ የጉሙሩክ ዲክላራሲዮን ሰነድ በመጠቀምና ዲክሌር በማስደረግ ገንዘቡን በማሸሽ በአቋራጭ ለመበልፀግ በመፈለግ በመንግስትና በህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ተብለው መጠርጠራቸውን ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አስታውቋል፡፡

በተጠርጣሪዎቹ ላይ በተጀመረው የምርመራ ስራ 16 የሰው ምስክር ቃል መቀበሉን ፖሊስ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አብራርቷል፡፡

በህገወጥ መንገድ የተመዘገበ የውጭ ምንዛሬ ገንዘብ ለምን አገልግሎት እንደዋሉ የደረሰውን የጉዳት

ከሙስና ምርመራ ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# ሳይቃጠል በቅጠል ...

አስፈላጊነቱና አዋጭነቱ ሳይረጋገጥ በሚፈጸም ግዥ ለመጠቀም ሲባል ይታቀዳል:: በቅድሚያ ከአቅራቢው ድርጅት ጋር በመነጋገር የግዥ ዕቅድ ይታቃዳል::

ሌላው የአቅራቢ መረጣ ነው:: በዚህ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ዝርዝር መግለጫ ከአቅራቢ በመውሰድ የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ማድረግ፣ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛ መሥፈርት ለአንድ አቅራቢ በሚያመች መልኩ ማዘጋጀትና ጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት፣ የጨረታ ማስታወቂያን ለሁሉም ተጫራች ተደራሽ አለማድረግ፣ ቀደም ሲል ለተጫራች ግልጽ ባልተደረገ መሥፈርት ተጫራች ለማውዳደርና ከውድድር ውጪ ለማድረግ መሥራት የግዥ ሙስና ሥጋት ነው::

ጨረታው ከወጣ በኋላ ዝቅተኛ የቴክኒክ ግምገማና በከፍተኛ የፋይናስ ግምገማ ውጤት ያመጣውን ተጫራች መምረጥ፣ በቴክኒክ ግምገማ ውስጥ የማይፈልጉትን ለመጣል እንዲያመች በትክክለኛ የሂሳብ ስሌት መሠረት አለማወዳደር ወይም የተወሰኑ የሂሳብ ስሌቶችን መዝለል እና በዝርዝር መግለጫ መሠረት ያልቀረበውን ተጫራች አሸናፊ የማድረግ ተግባር ሙስና ለመፈጸም እንዲያመች ይከናወናሉ::

ጨረታው ያሸነፈው አቅራቢ ቀደም ሲል ባቀረበው ናሙና መሠረት የማይመሳሰል ዕቃ እንዲያስረክብ ማድረግ፣ አቅራቢ በውል ስምምነት መሠረት በተቀመጠው ገደብ ዕቃውን ወይም አገልግሎትን ሳያስረክብ ሲቆይ ዝምታን መምረጥ፣ ጥራት የሚጎላቸውን ዕቃዎች የመረከብ ተግባራት ሙስና ለመፈጸም የሚተገበሩ ናቸው::

በመጨረሻም ከመመሪያ ውጪ በቂ ማስያዣ ሳያቀርብ ቅድሚያ ክፍያ መፈጸም እና እቃውን ሳያስረክብ ክፍያ መፈጸም የመሳሰሉት ተግባራት ይከናወናሉ::

በሌላ በኩል በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ድርጅት ግዥ መፈጸም፣ ያለበቂ ምክንያት በውስን ጨረታ ግዥን መፈጸም፣ በተደጋጋሚ የዋጋ ማወዳደሪያ በመጠቀም ግዥ መፈጸም፣ ያለበቂ ምክንያት ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም እና አቅራቢ ድርጅትን በብራንድ በማወዳደር ጨረታ አሸናፊ የመለየት ሂደት ሙስናን ለመፈጸም የሚተገበሩ ናቸው::

በመጨረም የዕቃዎችን አስፈላጊነት በቅድሚያ ሳይረጋገጡ ግዥ መፈጸምና ለዝናብና ፀሐይ ሜዳ ላይ የመጣል ሁኔታዎች ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመፈፀም የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው::

### በሀገራችን ስሙስና መከሰት ምክንያቶች

ሙስና የሚፈጸመው ሙስና ለመሥራት የተመቻቸ ሁኔታ ሲኖር ነው:: ተቋም ውስጥ ያሉ ህጎችና መመሪያዎች ወቅታዊ ያልተደረጉና ያለውን ነበራዊ ሁኔታ የማያመለክቱ ሲሆን፣ አጋጣሚውን በመጠቀም የቆዩ ህጎችን በማጠቀስ ሙስና ይሠራል፤ ሙስና የሚፈፅም ሠው ለመቅጣት ጠንካራ ህግ ቢኖርም፤ የቅጣት ውሳኔ ብያኔ እንዲሰጥ የሚያቀርበው ጉቦ በመቀበል በትክክለኛ ወንጀል አንቀፅ አይከሰስም:: የሙስና ተጠርጣሪው ጉቦ ከከፈለ ባስከተለው ጉዳት መጠን የቅጣት ውሳኔ አይሰጥበትም፤ ነፃ ሁሉ እንዲወጣ ይደረጋል::

በተቋም ውስጥ ባልጠፋ ሰው ሠነድ የማዘጋጀት፣ የማረጋገጥና የማጽደቅ ሥራዎችን አንዲሰራ የተመቻቸ ሁኔታ ከተፈጠረለት በቀጥታ ሙስና ይፈጽማል:: ካልሆነም በገንዘብና ንብረት ላይ በዝምድና የተሳሰሩ ሰዎች የማዘጋጀት፣ የማረጋገጥና የማጽደቅ ተግባራትን የሚያከናወኑ ከሆነ ሙስና ይፈጽማሉ::

በተቋም ውስጥ የፋይናንስና ንብረት እንቅስቃሴ ላይ ወቅታዊ የኦዲት ሥራ የማይሠራ መሆኑን የሚረዱ ሰዎች ሙስና ይፈጽማሉ:: የሥነምግባር ዝቅጠት ያላቸው ሰዎች በትስስርና በትብብር ለክፍያዎች ትክክለኛ ሠነዶችን በማዘጋጀት ሙስና ይፈጽማሉ::

ሥነምግባር የሌላቸው ሰዎች ያልሠሩትን እንደሠሩ በማድረግ ክፍያ በመጠየቅ ሙስና ይፈጽማሉ:: የመንግስት አገልግሎት እንዲሠጡ የተመደቡ ሰዎች የሚቆጣጠራቸውና የሚከታተላቸው ከሌላቸው ወይም ከቅርብ ኃላፊያቸው ጋር በመመሳጠር ከተገልጋይ የተለየ ጥቅም ለማግኘት ተግተው ስለሚሠሩ ሙስና ይፈጽማሉ:: በተለይ ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ ላይ ለበርካታ ዓመታትን እንዲያገለግል የተፈቀደለት አመራር ከሌሎች ጋር በሚፈጥረው መላመድ ሙስና ይፈጽማል::

### ሙስና እንዴት መከላከል ይቻላል?

ሙስና ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል:: ሙስናን ለመከላከል ሙስናን ከሚፈጽሙ ሰዎች በዕውቀትና ልምድ መብለጥ የግድ ነው:: ለዚህ ደግሞ በሙስና መከላከል ክሂሎት ላይ በቂ ሥልጠና መውሰድ፣ ሙስና መከላከልን በተመለከተ በሙስና መከላከል ውጤታማ የሆኑ ሀገራትን ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መቀመርና መተግበር ያስፈልጋል::

ስለሆነም ሰዎች በሥነምግባርና በሞራል እሴት/ግብረገብ/ በመታነጽ ሙስና እንዲጠየፉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የአመለካከት ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ተደጋጋሚ ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው:: ስልጠናዎች የሥነምግባር ጥቅምና ሙስና ጎጅነትን በንጽጽር በማሳየት ቢሆን ይመረጣል::

በሌላ በኩል በተቋም ውስጥ የሙስና ሥጋት ያለባቸውን አሰራርና አደረጃጀት በመለየትና ደረጃ በመስጠት የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር ነው:: በተቋም በተለይ የገንዘብ እንቅስቃሴ ያለባቸው ወይም የንብረት ክምችት ያለባቸው ቦታዎች ላይ ሙስና ይሰራበታል::

የሥልጣን ክምችት ለአንድ ሠው መሥጠት ለሙስና በር የሚከፍት ነው:: ስለዚህ ለአመራርና ሠራተኞች የሥነምግባር ኮድ ማዘጋጀት፣ ግንዛቤ መፍጠርና አፈፃፀሙን ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣ ከሰው ንክኪ ነፃ የሆነ የዲጂታል አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፣ አንድ ሥራ ሂደት ካለው በተለያየ ሠው እንዲሠራ ማድረግ፣ ህግ፣ ደንብና መመሪያዎችን በየጊዜው ወቅታዊነትን መጠበቅ፣ ለሚሰጡት አገልግሎቶች የአገልግሎት ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣ ለተጠቃሚው ማስተዋወቅ፣ በተቋም ዕቅድ ክንውን ላይ ቀጣይነት ያለውና ያልተቆራረጠ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ እንዲሁም ሙስና ፈፃሚዎች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃዎችን መውሰድ የመሳሰሉትን መተግበር ሙስናን ለመከላከል ያስችላል::

በሀገሪቱ በመንግስት ሀብትና ንብረት የመወሰን ወይም የመጠቀም ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች የግላቸው ሀብትና ንብረት የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ ቢጣልባቸው ከመንግስት ሀብትና ንብረት እንዳይቀላቀል ዕገዛ ከማድረጉም በላይ በመንግስት አሰራር ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ይፈጥራል::

ከዚህ ባለፈ የተመዘገበው ሀብትና ንብረት መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ በማጣራት ምንጩ ያልታወቀ ሀብትና ንብረት በመለየት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ሙስና ከመከላከል አንፃር ፋይዳው ከፍተኛ ይሆናል::

ሶስተኛው የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን መቀበል፣ መመርመር፣ መክሰስና የተመዘበረ ሀብት ማስመለስ ነው:: ይህ ሥራ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ሀገራት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት አሠራር ነው:: በየቦታው የራሳቸው ያልሆነውን የመንግስት ሀብትና ንብረት ለመስረቅ ወይም ለመመዝበር ወይም ለማጭበርበር የሚጥሩ ሰዎችን የሚያዩ ወይም የሙስና ድርጊት በሚፈጸም አሠራር ሂደት ውስጥ ሆነው፣ የሚሆነውን የሚያውቁ ሰዎች ለመንግስት በድርጊቱ ታሪክ ላይ ጥቆማ እንዲያቀርቡ በጊዜው መነሳትና ግንዛቤ መፍጠር፣ የጥቆማ መቀበያ ቦታዎችን ከማንኛውም ዕይታዎች ነፃ በሆነ መልኩ ማመቻቸት ነው::

የሚቀርቡ ጥቆማዎችን ሚሥጥራዊነትንና ወቅታዊነትን በጠበቀ መልኩ የመመርመርና የመክሰስ ሥራዎችን በመሥራት የጠቋሚዎችን ልፋት ውጤታማ ማድረግ፤ ሌሎችም የሕብረተሰብ አካላት ከዚህ ተሞክሮ በመውሰድ ያዩትንና የሰሙትን የሙስና ወንጀል ተግባራትን እንዲጠቅሙ ያነሳሳል:: እንዲሁም ለጠቋሚዎችና ለምስክሮች ከለላ የመስጠት ሥራ በልዩ ትኩረት ማከናወን ያስፈልጋል::

አራተኛው ሙስና ያለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሊሳካ ስለማይችል ብሄራዊ የቅንነት አሠራር በማደራጀት የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋርና ተባባሪ እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: ሁሉም የባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡ እያንዳንዱ የባለድርሻ አካል ምን ተግባር መፈጸም እንዳለበት ግልጽ የሆነ የፀረ-ሙስና ፖሊስ ማዘጋጀትና ማጽደቅ እንዲሁም በህግ ማዕቀፍ ማስደገፍ የግድ ይላል::

ለፀረ-ሙስና ትግል እንደባለድርሻ የሚወሰደው የህግ አውጪ፣ አስፈፃሚ፣ ህግ ተርጓሚ፣ የፍትህ አካላት፣ የዋና ኦዲተር፣ የተቋማት፣ የተፎካከሪ ፓርቲ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ ሚዲያዎችና የዕንባ ጠባቂ እንዲሁም የመሳሰሉት የፀረ-ሙስና ትግል አካል በማድረግ ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል::

በተለይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በህዝብ ተወካይነታቸው አባሎቻቸው በሥነምግባርና የሞራል እሴቶች በመታነፅ ሙስና እንዲከላከሉና እንዲታገሉ ማብቃት፣ የፀረ-ሙስና ተቋም በህግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትን በተገቢው ስለመወጣቱ እንዲሁም ሀገሪቱን የሚያስተዳድረው መንግስት የሀገሪቱን የልማት ዕድገት የሚያሰናክለውን ሙስና በቁርጠኝነት እንዲከላከልና እንዲዋጋ የመነሳሳትና ድክመቶች ካሉ ደግሞ በየጊዜ ግምገማ በማካሄድ ምክረ ሀሳብ ጭምር በመስጠት ትግሉን ማጠናከር ይጠበቅበታል::

አምስተኛው የአህጉርና አለም አቀፍ ትስስሮችን ማጠናከር ነው:: ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የሙስና መከላከል ስምምነት ሠነድ መሠረት የህብተሰብና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማጠናከርና ሚናን ማሳደግ ይጠበቃል:: በተለይም ከሀገር የሚሸሸውን ሀብት ለማስመለስ የመረጃ ልውውጦችን ለማድረግ እንዲሁም የተሻለ አፈፃፀም ካለቸው የፀረ-ሙስና ተቋማት ልምድና ተሞክሮ ለማግኘት ትብብርና ትስስር ለማጠናከር ጠቃሜታው የጎላ ነው::

በአጠቃላይ ሙስና የሀገር እድገት ፀር ነው:: በጣም ጥቂት የሆኑ ሰዎች ሲከብሩ ብዙሃኑን በድህነት ማቅ ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋል:: ሁሉም ሰው ሌብነትን በመተው ለሀገር እድገት ቢረባረብ ሀገር ታድጋለች፣ ትበለጽጋለች::

ነገር ግን ጥቂቱ ለሀገር ተቆርቋሪ ሲሆን፤ የተወሰኑት ደግሞ ለሀገር ሳይሆን ለራሳቸው ብቻ ለማደግ የሚረባረቡ ከሆነ የመጨረሻ ውጤቱ ውድቀት ነው:: ስለሆነም የመጀመሪያ መብትን በገንዘብ ለማግኘት ጥረት አለማድረግ፣ መብትን ለመውሰድ ሲኬድ ገንዘብ የሚል ካለ ለሚመለከተው አካል መጠቆም፣ የመንግስትንና ህዝብን ሀብትና ንብረት ለመሥረቅ የሚሠሩትን መታገልና መከላከል ከቻልን ሀገራችን ከየትኛውም ሀገር አታንስም፤ ታድጋለች፤ እኛም በጣም ጥሩ ኑሮ ይኖረናል:: እኛ በፈለግነው ልክ እንኳን መኖር ባንችል ለልጆቻችን በጣም ጥሩ ኑሮ ለመኖር የሚያበቃ ሀገር ለትውልድ እናስረክበለን::

# ከሙስና ምርመራ ...

መጠን ምን ያክል እንደሆነ የባለሙያ ማብራሪያ መቀበሉንም ገልጿል።

በተጨማሪም ከጉሙሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሰነዶችን ማሰባሰቡን ጠቅሷል። ቀሪ ስራዎች ማለትም ከመንግስታዊ ተቋማት፣ ከብሔራዊ ባንክና ከሌሎች የተለያዩ ባንኮች በጉዳዩ ዙሪያ ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ እንደሚቀረው ገልጾ ተጨማሪ 14 ቀን የምርመራ ጊዜ እንዲፈቀድለት ጠይቋል።

መዝገቡን የተመለከቱት ዳኛ የተጠርጣሪዎች የተሳትፎ ደረጃቸው ተለይቶ እንዲገለጽ የጠየቁ ሲሆን፥ መርማሪ ፖሊስ 1ኛ ተጠርጣሪ 100 ሺህ ዶላር፣ 2ኛ ተጠርጣሪ 150 ሺህ እንዲሁም 3ኛ ተጠርጣሪ ደግሞ 242 ሺህ 658 የአሜሪካ ዶላር በተናጠል በአቋራጭ አሸሽተዋል በማለት ጠቅሶ ለይቶ አቅርቧል።

ተጠርጣሪዎቹ ከጠበቃቸው ጋር ቀርበው በፖሊስ የተጠቀሰውን ወንጀል ድርጊት እንዳልፈጸሙ ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን፥ የዋስትና መብታቸውም እንዲከበር ጠይቀዋል።

የጊዜ ቀጠሮ መዝገቡን አስቀርበው የተመለከቱት የችሎቱ ዳኞች የተጠርጣሪዎቹን የዋስትና ጥያቄ ለጊዜው ውድቅ በማድረግ ፖሊስ ከጠየቀው የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ ውስጥ የ11 ቀናት የምርመራ ጊዜን ፈቅዷል::

በመጨረሻም በአዲስ አበባ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ 72 ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሕጋዊ የይዞታ ባለቤት እያለ ለሌላ ለማይገባው ግለሰብ 500 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ አድርገዋል የተባሉ 8 ተከሳሾች የጥፋተኝነት ፍርድ ተላለፈባቸው።

1ኛ ተከሳሽ በቀድሞ የቦሌ ክ/ከተማ በአሁኑ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ የወረዳ 15 አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ የነበሩት ሽመልስ ዘውዱ የጥፋተኝነት ፍርድ ከተሰጠባቸው መካከል ይገኙበታል::

2ኛ የአርሶ አደር ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበሩት ቢፍቱ ደረሰ፣ ከ3ኛ እስከ 5ኛ በአርሶ አደር ኮሚቴነት የተጠቀሱ ሰለሞን ሁንዴሳ፣ ጌታቸው አሰፋ እና ተስፋዬ ሽብሩ ዳፋ እንዲሁም 6ኛ ተከሳሽ በቀድሞ የቦሌ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር የልኬትና ካርታ ዝግጅት ባለሙያ የሆኑት ቤተልሄም ወ/ጊዮርጊስ ይገኙበታል ተብሏል::

በተጨማሪም 7ኛ ተከሳሽ በቀድሞ የቦሌ ክ/ከተማ የሕግና ሰነድ አጣሪ ባለሙያ ህይወት ታደሰ ሳህሌ፣ 8ኛ ተከሳሽ የይዞታ ካርታ በሕገወጥ መንገድ ተዘጋጅቶለታል የተባለው አሸናፊ ጥላሁን ናቸው።

ተከሳሾቹ የአርሶ አደር የይዞታ ካርታ ከመሰራቱ በፊት በይዞታው ካርታ የሚሰራለት ግለሰብ በይዞታው ላይ ነባር አርሶ አደር መሆኑንና ይዞታው ላይ ቤት ሰርቶ እንደሚኖር ሕጋዊ መሆኑን ጭምር እንዲያረጋገጥ አስተዳደሩ በ2010 ዓ.ም በ6ኛው የሊዝ ጉዳይ ላይ ያስተላለፈውን ውሳኔ ባለመከተል ሕጋዊ የይዞታ ባለቤት እያለ ለማይገባው ግለሰብ የ500 ካ/ሜትር ይዞታ ካርታ በየካቲት 19 ቀን 2012 ዓ.ም እንዲሰጠው አድርገዋል ተብለው የተከሰሱ ናቸው።

በቀረበባቸው ክስ እንደተመላከተው÷ 1ኛ ተከሳሽ ሕጋዊ የይዞታው ባለቤት ወ/ሮ ዘውዲቱ ገመቹ እያሉ ከሕግ ውጪ ከ8ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር 500 ካ.ሜ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለ8ኛ ተከሳሽ እንዲሰጥ አድርጓል ተብሎ በክሱ ተጠቅሷል።

ከ2ኛ እስከ 5ኛ የተጠቀሱ ተከሳሾች÷ የአርሶ አደር ኮሚቴ ሰብሳቢና አባል ሆነው ሲሰሩ ይዞታው ላይ ቤት ሰርቶ የሚኖር ሕጋዊ ባለቤት መኖሩን እያወቁ የይዞታው ባለቤት ላልሆነ ለ8ኛ ተከሳሽ የይዞታው ባለቤት ነው ብለው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አስደርገዋል ሲል ዓቃቤ ሕግ በክሱ አስረድቷል።

6ኛ ተከሳሽ ካርታ ለሚሰራለት ግለሰብ ካርታው ከመሰራቱ በፊት አስቀድመው በመስክ ልኬት ማረጋገጥ ሲገባቸው 8ኛ ተከሳሽ የይዞታው ባለቤት እንዳልሆነ እያወቁ በወቅቱ በነበረው የሊዝ ግምት 1 ሚሊየን 63 ሺህ 83 ብር የሆነ 500 ካ.ሜ የይዞታ ሰርተፍኬት አዘጋጅተዋል ተብለው በክሱ ተጠቅሰዋል።

7ኛ ተከሳሽም የሰነዱን ሕጋዊነት ባለማረጋገጥ 8ኛ ተከሳሽ የራሱ ያልሆነ ይዞታን የኔ ነው ብሎ የ500 ካ.ሜ የይዞታ ማረጋገጫን ያለአግባብ በመውሰድ በሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦባቸው ነበር ተብሏል።

3ኛና 6ኛ ተከሳሾች ክሱ ከደረሳቸው በኋላ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አልፈጸምንም ብለው የዕምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተው እንደነበርም ተጠቁሟል።

ሌሎቹ ተከሳሾች በሌሉበት ጉዳያቸው የታዬ ሲሆን÷ ዐቃቤ ሕግ ለወንጀሉ መፈጸም የሚያስረዱ ምስክሮችንና ሕጋዊ የይዞታ ባለቤት የሆኑ ግለሰብን የገጠር መጠቀሚያ ግብር የከፈሉበትን ደረሰኝና ሌሎች ማስረጃዎችን አይይዞ አቅርቧል።

ችሎቱ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ የምስክሮችን ቃል ከመረመረ በኋላ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሾቹ በተገቢው መከላከል ባለመቻላቸው በአብላጫ ድምጽ በእለቱ ቀጠሮ የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል። ችሎቱ በተከሳሾቹ ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት የተገኘው መረጃ ያስረዳል::

# ኪነ-ጥበብ

ይድረስ ለኛ

## ይድረስ ለኛ

ይድረስ ለእኛ ለኔና ላንተ

ዘመን በትውልድ ክር ባንድ ስቦ ላቋጠረን

የዚያ ሰፈር ኤሊቶች፣ የዚህ ሰፈር ኤሊቶች እየተባባልን

በህዝብ ስም እየማልን፣ በወገን ስም እየማልን

አገር አቃጥለን ለምንሞቅ

በእናቶች ሃዘን ሰቆቃ፣ በአባቶች እንባ ለምንስቅ

ይድረስ ለእኛ ለኔና ላንተ

ለነቃነው ለበቃነው

ክፉ ዘመን ክፉ ሥርአት፣ በጥፋት ላስተሳሰረን

በጥላቻ የተሰራ፣ በቂም በቀል የበቀለ ሴራና ሸፍጥ ለወረረን

ክህደት- ቅጥፈት- መሰሪነት፣ የህሊና አይናችንን ልባችንን ለሰወረን

ከሰው ተራ ወርደን ከፈጣሪ ተገዳድረን

ሃገር ሸቅብ የምትረጨው እንባ የማይገደን

ይድረስ ለእኛ ለኔና ላንተ

አክቲቪስት በሚባል ማዕረግና ካባ ተጠቅልለን

ከአገር በላይ … ከህግ በላይ… ተቆልለን

ሰዎችን ከኑሮ ነቅለን፣ ፍትህን ጫማችን ስር ጥለን

በአገር ላይ ፍቅርን መግደል ፤ ተስፋን መግደል፤ ደስታን መግደል፤ ሰላምን መግደል

እንደ ውሃ ጥም ለቀቀለን….ይመስለኛል ለኔና ላንተ

ድንቁርና፣ ዕብሪት፣ ትዕቢት፣ ክፋት ላስታጠቀን

ነገ ታሪክ በእውነት ችሎት በደም ቃል ለሚጠይቀን

ወንድምዬ፤ ምን መልስ አለህ?--

በጌትነት እንየው

# መልካም ዜጋ

## የመልካም ሥነምግባር አርዓያ ፕሬዘዳንት

**በከድር ጀማል**

"በማገኘው የገቢ መጠን ልክ ተደስቼ እኖራለሁ!" ጆሲ ሙጂካ- የቀድሞ ኡራጋይ ፕሬዘዳንት።

የራስን ጥቅም ከህዝብ ጥቅም አስበልጦ ማየት እንደ ስልጣኔና አዋቂነት በተቆጠረበት በዚህ በያዝነው ክፍለ ዘመን ውስጥ የራስን ጥቅም ወደ ጎን በመተው የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም የሀገር መሪ ማግኘት በእርግጥም መታደል ነው።

ብታምኑም ባታምኑም የዓለማችን ድሃ ፕሬዘዳንት ማን ነው? (Who is the Poorest President in the World?) ብላችሁ ጎግልን (google.com) ብትጠይቁ ማንንም ሳይሆን በቀጥታ የሚጠቁማችሁ እርሶ አደሩን የቀድሞ የኡራጋይ ፕሬዘዳንት ጆሲ ሙጂካን ነው።

አብዛኞቻችን ለክብራችንና ለአኗኗር ዘይቤያችን እንጨነቃለን፤ ለፕሬዘዳንት ጆሲ ግን ይህ ምናቸውም አይደለም። ለእሳቸው ትልቁ የህሊና እርካታ የሀገራቸው ህዝብ መሠረታዊ ህይወት ተለውጦ ማየት ነው።

ጆሲ የደቡብ አሜሪካ አህጉር አንዷ የሆነችውን ኡራጋይ 40ኛው ፕሬዘዳንት በመሆን ከ2010 እስከ 2015 እ.ኤ.አ. የመሩ መሪ ሲሆን፤ የሀገራቸውን ህዝብ ልብ እንዴት ሊገዙ ቻሉ? ከሌሎች የዓለማችን ሀገር መሪዎችስ ምን የተለየ ነገር ፈፅመው ነው የዓለማችን ትላልቅ መገናኛ ብዙሃን ልዩ ትኩረትና አድናቆት የቸሯቸው? የሚሉ ጥያቄዎች በሁሉም ሰው አዕምሮ መመላለሱ አይቀርም።

በእርግጥም ፕሬዘዳንት ጆሲ ሙጂካ (Jose Mujica) ስልጣን ላይ በነበሩባቸው አምስት ዓመታት ከሌሎች የሀገራት መሪዎች ለየት የሚያደርጋቸው ዓለምን የተመለከቱበት መንገድ የተለየ በመሆኑ ነው።

"የኔ ደስታ የሚመነጨው በዙራዬ ካሉ ሰዎች ደስታ ነው" በሚለው መርሃቸው መሠረት ለሰው ልጅ ሰብዓዊ ክብር ቅድሚያ በመስጠት፣ የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆዎች የሆኑትን ታማኝነትና ሀቀኝነት በተግባር በመፈጸም እንዲሁም በህዝብ የተሰጣቸውን ስልጣንን በአግባቡ በመገልገል ለሌሎች መሪዎች አርዓያ በመሆናቸው ነው።

ጆሲ ሙጂካ በአኗኗር ዘይቤያቸው ቀለል ያለ ኑሮን የሚመርጡ በመሆናቸው ለፕሬዘዳንትነት በተደረገው ምርጫ ተወዳድረው እንዳሸነፉ ምንም ዓይነት የቅንጦት ኑሮ ሳያምራቸው መንግስት የሰጣቸውን ቤተ-መንግሥት መኖሪያ በመተው ገጠር ውስጥ በሚገኘው የግል መኖሪያ ቤት ውስጥ የኖሩ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1978 የተመረተችውን አሮጌ ሰማያዊ ቮልስ ዋገን መኪና "ህይወቴ ናት" በማለት ማሽከርከራቸውን ቀጠሉ።

የሀገሪቱ መንግስት ለደህንነታቸው ብሎ ፖሊስ ሲመድብላቸው፣ "እኔ የደህንነት ሥጋት የለብኝም!" በማለት ምንም ዓይነት ጥበቃ እንደማይፈልጉ ቢገልጹም፤ ለሀገር ደህንነት ሲባል ሁለት የፖሊስ መኮንኖችና 'ማኑኤላ' ተብላ የምትጠራ ባለ ሶስት እግር ውሻ ለጥበቃ ተመድበውላቸው ነበር።

በአንድ ወቅት ለምን በቤተ-መንግሥት አይኖሩም ተብለው ሲጠየቁ፣ "አብዛኛው የዓለማችን መሪዎች የስልጣን እርካቡን ከረገጡ በኃላ ለመረጣቸው ህዝብ መሪ መሆን ሲገባቸው ወዲያውኑ ንጉስ ይሆናሉ። ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል አይገባኝም፤ እኔ እንደሚገባኝ ግን ማንም ሰው ወደ ስልጣን ሲመጣ ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል መሆኑን መቀበልና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነቱን መቀበል ነው።

የምናዝበት ሀብት እና ንብረት የማን መሆኑን መረዳት ይገባናል። ስልጣን ላይ ሲወጣ ወዲያውኑ ምቹና ሰፋፊ ክፍሎች ያሉት ቤተ-መንግሥት፣ ቀይ ምንጣፍ፣ የቅንጦት ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በርካታ ሰዎች ከኋላ እየተከተሉ 'አቤት፣ጌታዬ!' ይሉሃል።

ይህ ሁሉ ለኔ ከንቱ ነው። ለኔ የህሊና እርካታና ደስታ የሚሰጠኝ የምኖርበት ቤትና የማሽከረክረው መኪና ሳይሆን እንዳገለግለው የመረጠኝ ህዝብ ቀደም ሲል ከነበረበት ህይወት የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው" በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል።

የፕሬዜዳንት ጆሲ ልብሶች የሚታጠቡት በእጅ ሲሆን፤ የሚጠቀሙት ውሃ ከጉድጓድ የሚወጣ ነው። የሚመገቡት ምግብም በአብዛኛው ከባለቤታቸው ጋር ገጠር ውስጥ ከሚገኘው የእርሻ ማሳቸው የተገኘ ነው። ባልና ሚስቱ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን አብዛኛውን ገቢ የሚያገኙት በጋራ ከሚሰሩት የአበባ እርሻ ልማት ነው።

"የህዝብን ሀብትና ንብረት ለግል ጥቅሜ ለማውል ስልጣን የምይዝ ከሆነ ሀገሪቱን ምኑን ጠቀምኳት?" በማለት ከጠየቁ በኋላ አያይዘውም፤ "እንደወረርሽን እየተዛመተ የመጣውን ኃላ ቀር አመለካከት መዋጋት አለብን። ድሃ ማለት በህይወቱ ውስጥ ሁልጊዜ የበለጠ ለማግኘት ሳያቋርጥ የሚተጋ ማለት እንጂ ብዙ ሀብትና ንብረት የሌለው ሰው ማለት አይደለም" በማለት በተደጋጋሚ አቋማቸውን ከመግለጽ አልተቆጠቡም።

ሌላው ፕሬዜዳንቱን በሀገራቸው ህዝብ ምንጊዜም እንዳይረሱና በህዝቡም ከፍተኛ ድጋፍ ያስገኛላቸው ነገር ቢኖር፤ ከሚያገኙት ወራዊ ደመወዛቸው አብዛኛውን ማለትም 90 በመቶ ወይም 12 ሺህ የአሜሪካ ዶላር የሚሆነውን ገንዘብ ለድሃው ህብረተሰብ ገቢ በማድረጋቸው ነው።

የጆሲ የበጎ አድራጎት ማህበር ድጋፍ የሚያደርገው በዝቅተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ የህብረተሰብ ክፍሎችና አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን በማቅረብ የገንዘብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የፈጠራ ባለሙያዎች ነው።

'ይህን ያህል በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ለምን ለእርዳታ ድርጅት ለመስጠት ተነሳሱ?' ተብሎ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ "ሀገሬ ለኔ የምትሰጠኝ ገንዘብ ከሚያስፈልገኝ በላይ ነው። ይህን ያደረኩት ደግሞ መስዋትነት ለመክፈል ሳይሆን የዜግነት ግዴታዬ በመሆኑ ነው" በማለት መልሰዋል።

ከዚህም በተጨማሪ በኡራጋይ ውስጥ ኢኮኖሚ ዕድገቱ ተከታታይና ዘላቂነት ያለው እንዲሆን በማድረግ ጤናማ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲዘረጋ መሠረት በመጣልና በወቅቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ድህነት ከ37 በመቶ ወደ 11 በመቶ ዝቅ በማድረግ እንዲሁም በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መጠን የሥራ አጥ ቁጥርን በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ለሌሎች መሪዎች አርዓያ የሆኑ መሪ በመሆናቸው ነው።

ጆሲ ጦርነትና ግጭትን አምርሮ በመጥላት ውይይትና ድርድርን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው የሚለውን አቋም በማራመድ የሚታወቁ መሪ ናቸው። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው በአሜሪካ ታዋቂው ሀርቨርድ ዩንቨርስቲ በመገኘት ባደረጉት ንግግር፣ "ዓለማችን በደቂቃዎች ውስጥ ለጦር መሣሪያ ግዢ ሁለት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ታወጣለች፤ ይህ ሁሉ ገንዘብ የሚፈሰው አስፈላጊ ለሆኑ ጦርነቶች ሳይሆን እንዲሁ በከንቱ ለሚካሄዱ ግጭቶች ነው።

በኔ በኩል ከጦርነት በፊት ቅድሚያ የምሰጠው ለድርድር ነው። እጅግ መጥፎ ድርድር በጣም ጥሩ ከሚባል ጦርነት ይሻላል። ስለዚህ ሰላምን ለማረጋገጥ መቻቻልን ኮትኩተን ልናሳድገው ይገባል" በማለት ለዩንቨርስቲ ተማሪዎች መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ቢቢሲ (BBC) የተባለው የእንግሊዝ ዜና ማሰራጫ ጣቢያ እ.ኤ.አ. በ2012 ለፕሬዜዳንቱ ቃለ-መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር። ስለ ድህነታቸው ተጠይቀው ሲመልሱ፣ "የዓለም ድሃው ፕሬዘዳንት ተብዬ እጠራለሁ፤ ነገር ግን እኔ ድሃ ፕሬዘዳንት እንደሆንኩ አይሰማኝም። ፕሬዘዳንት በመሆኔ ቀደም ሲል ከነበረው የኑሮ ዘይቤ የምቀይርበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ምክንያቱም የተመረጥኩት ህዝብ ለማገልገል እንጂ በህዝብ ለመገልገል አይደለም። በእርግጥ ቀለል ያለና ወከባ ያልበዛበት ህይወትን እመርጣለሁ፤ በህይወት ለመኖር በጣም ትንሽ ነገር ነው የሚያስፈልገኝ። በኔ በኩል ድሃ ብዬ የምጠራቸው



ጆሲ ሙጂካ (Jose Mujica)

ሰዎች እጅግ የተደላቀቀ ህይወትን ሁልጊዜ በመፈለግ በርካታ ሀብትን ያለ አግባብ ለማካበት የሚጥሩ ሰዎችን ነው" በማለት ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል።

በአንድ ወቅት ታዋቂ በሆነው የአሜሪካን የቴሊቪዥን ጣቢያ ሲ ኤን ኤን (CNN) የስፓንሽ ቋንቋ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ አድርገው፤ ጋዜጠኛው "ሀብታም ሰዎችን ይጠላሉ ይባላል፤ ለመሆኑ ይህን አስተያየት እንዴት ይመለከቱታል?" በማለት ጠይቋቸው ነበር።

"እኔ ብር ያላቸውን፣ብር የሚወዱና በብር ያበዱ ሰዎችን አልጠላም፤ ነገር ግን በፖለቲካ መርህ መሠረት ገንዘብና ፖለቲካ መለያየት አለባቸው። ፖለቲካን መሠረት አድርገን ገንዘብ ለማግኘት የምንሮጥ ከሆነ አደጋው የከፋ ይሆናል" በማለት ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል።

አያይዘውም "ገንዘብን የሚያመልኩ ሰዎች ከፖለቲካ ጨዋታ መውጣት አለባቸው፤ ምክንያቱም አደገኞች ናቸው። ገንዘብን አብዝተው የሚፈልጉ ሰዎች በሌሎች የሥራ ዘርፍ በመሳተፍ ሀገር ማገልገል ይጠበቅባቸዋል እንጂ በህዝብ በመገልገል ገንዘብ ለመሰብሰብ መሞከር ጉዳቱ የከፋ ይሆናል።

ፖለቲካ ከፍተኛ ትግል ተደርጎበት የሚገኝና አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል የምታስደስትብት የአስተዳደር ጥበብ ነው" በማለት አቋማቸውን አሳውቀዋል።

ጆሲ ሙጂካ በስልጣን ዘመናቸው ከሀገራቸው አልፈው ለዓለም ህዝብ እኩልነት፣ ሰላም፣ ነጻነትና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል የሚቆረቆሩ መሪ ነበሩ።

በአንድ ወቅት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በዘላቂ የልማት መርሃ-ግብር ዙሪያ ባዘጋጀው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ተገኝተው የተናገሩት ንግግር ይደነቅላቸዋል። "በዛሬው ከሰዓት በኃላ ውሏችን ድህነትን ከምድራችን ላይ ለማስወገድ ስለ ዘላቂ የልማት ጉዳይ ተወያይተናል፤ ነገር ግን በአዕምሯችን ምን እያሰብን ይሆን? ከሀብታም ሀገራት የልማትና የሀብት አጠቃቀም ሞዴል ለመውሰድ ነው የተሰባሰብነው? እኔ የምጠይቃችሁ አንድ ነገር አለ? የጀርመን ህዝብ በቤተሰብ ደረጃ ያለው የመኪና መጠን የህንድ ህዝብ በቤተሰብ ደረጃ ቢኖረው፡- ይህች ምድራችን በአካባቢ አየር ብከላ የተነሳ ምን ያህል የኦክስጅን መጠን ይቀረን ነበር?" በማለት በጉባኤ ላይ ለታደሙት ጉባይተኞች ጥያቄ አቅርበዋል።

ንግግራቸውን በመቀጠል "ስለዚህ ዓለማችን ያላት ሀብት ለ7 ቢሊየን ወይም ለ8 ቢሊየን ህዝቦቿ በቂ መሆን ሳይችል ቀርቶ ሳይሆን ጥቂት የዓለማችን ሀብታም ሀገራት የብዙሃኑን ድሃ ሀገራት ሀብት ያለ አግባብ በመጠቀማቸውና ምድራችንን በመጉዳታቸው ነው" በማለት ሀሳባቸውን በግልጽ ተናግረዋል።

በኡራጋይ ህዝብ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያገኙት የቀድሞው ፕሬዜዳንት ጂሲ ሙጁይካ በህዝቡ ተመራጭ በመሆን እንደገና ቢመረጡ ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚኖራቸው ቢታመንም፤ በሀገሪቱ ህገ-መንግስት መሠረት እንዲሁም ከዕድሜ አንጻር ተመዝኖ እ.ኤ.አ. በ2014 በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ ሳይሳተፉ ቀርተዋል።

ጆሲ ሙጂካ መልካም ሥነ-ምግባር በመላበስ የህዝብን አደራ በታማኝነት በመፈፀም፣ በሀገራቸው ውስጥ መልካም አስተዳደር በማስፈን፣ በተለይ ለሰው ልጅ መልካም ግንኙነት ለፍቅር፣ ለወንድማማችነት በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የሀገሪቱ ዜጎች በአጠቃላይ ለዓለም ህዝብ በአበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ከነበሩት ባራክ ኦባማ፣ ከቻይናው ፕሬዘዳንት ጂንፒንግ (Jin Ping) እና ከቀድሞ የብራዚል መሪ ክሪስቲና ኪሪችነር (Cristina Kirchner) እንዲሁም በርካታ የአውሮፓና የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት መሪዎች በከፍተኛ ክብር ሀገራቸውን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበውላቸው ጥሪውን ተቀብለው የጎበኙ ሲሆን፤ በተገኙባቸው ሀገራት ውስጥ ለሚገኙ የሀገራቱ መሪዎችና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከተለያዩ የደቡብ አሜሪካ ሀገራት የክብር ኒሻኖችና ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል። ከነዚህ ሀገራት መካከከል ፓራጎይ፣ ፔሩ፣ ሜክሲኮ፣ ኤኳደርና ኩባ በግንባር ቀደምትነት ሽልማቱን ለቀድሞ ኡራጋይ ፕሬዘዳንት ጆሲ ሙጂካ ያበረከቱ ሀገራት ናቸው።